EEA/EEPRI

Ethiopian Economic Association/ Ethiopian Economic
Policy Research Institute
Tel. 251-1- 55 74 59, 251-1 12 80 77
Fax No. 251-1 56 52 52
P.O.Box 34282, A.A Ethiopia:
e-mail: eea@telecom.net .et

EEA/EEPRI

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር/
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

# የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር በኢትዮጵያ

ለድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ሰነድ ዝግጅት
ስልጠና የተዘጋጀ

በወ/ሮ ጥሩወርቅ ትዛዙ

መስከረም 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| እርዕስት | ገጽ |
| --- | --- |
| የቃላት ትርጉም | |
| መግቢያ | 1 |
| 1. የመንግስር በጀትና የድህነት ቅነሳ ግንኙነት | 3 |
| 2. በጀት ምንድነው? | 7 |
| 2.1 የበጀት አስፈላጊነት | 7 |
| 3. የበጀት ሥርዓት በኢትዮጵያ | 9 |
| 4. የበጀት አቋም | 10 |
| 4.1 የገቢ በጀት | 10 |
| 4.1.1 የአገር ውስጥ ምንጮች | 10 |
| 4.1.1.1 ታክስ | 11 |
| 4.1.1.2 ታክስ ያልሆኑ ምንጮች | 16 |
| 4.1.1.3 ካፒታል በጀት | 17 |
| 4.1.2 የውጭ አገር ገቢ /ብርድና እርዳታ/ | 18 |
| 4.2 የወጪ በጀት | 22 |
| 4.2.1 መደበኛ በጀት | 22 |
| 4.2.2 ካፒታል በጀት | 30 |
| 5. የበጀት ምድብ | 37 |
| 6. የዕቅድና የበጀት ጊዜ | 40 |
| 7. የመንግስት ሂሳብ አቀራረብ ቁጥጥር | 49 |
| 8. የበጀት አስተዳደር ሥርዓት ከሕግ አንፃር | 52 |
| 8.1 ሕግ መንግስት | 52 |
| 8.2 የፋይናንስ አስትዳደር አዋጅ | 53 |
| 9. የአልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር በኢትዮጵያ | 55 |
| 9.1 የገቢ ክፍፍል | 55 |
| 9.2 የክልሉች ድጎማ | 58 |
| 9.3 በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን የአወባል ወረዳ የበጀት አመዳደብ | 61 |
| 10. የመንግስት የእቃና የአገልግሎት ግዥ አጠቃላይ ገጽታዎች | 64 |
| 10.1 የግዥ ዓላማዎች | 65 |
| 10.1.1 ቁጠባ | 65 |
| 10.1.2 ቅልጥፍናና ብቃት | 66 |
| 10.1.3 ከአድልዎ ነፃ የሆነ አሠራር መፍጠር | 66 |
| 10.1.4 ግልጽነት | 66 |
| 10.1.5 ለህዝብ ተጠያቂነት | 67 |
| ማጠቃለያ | 68 |

## የቃላት ትርጉም

- በጀት መፍቀድ ከተጠቃለለው ገንድ ውስጥ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ለመክፈል የሚያስችል የሕግ ስልጣን ነው።
- የበጀት ጥሪ የመንግስር መ/ቤቶች ዓመታዊ የበጀት ጥያቄአቸውን እንዲያቀርቡ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በጋር በጽሑፍ የሚያስተላልፉት ጥያቄ ነው።
- የበጀት ምድብ የበጀት ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው።
- የወጪ ማዕከል የበጀት አስተዳደር ወይም ኃላፊነት ክፍል ሲሆን፣ በጀቱን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት ክፍል የተመደበለትን በጀት ስምንት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ማስገኘት በሚችል መንገድ የሚመራበት ነው።
- የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ በዕቅድ እና በበጀት አፈታቀድ ሂደት የሚታለፉ ተግባሮችን እና ኃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ነው።
- የፋይናንስ ዕቅድ የመጪውን ዓመት ወጪ እና የፋይናንስ ምንጭ የሚያሳይ ዓመታዊ ዕቅድ ነው።
- የመንግስት ኢንቨስትመንት ኘሮግራም የመንግስት ኘሮግራም የጥቅል ሀብት ጠቋሚ ዕቅድ እሀዞች በመጠቀም የሚዘጋጅ የካፒታል ወጪ የሶስት ዓመታት ተንከባላይ ዕቅድ ነው።
- የተደገፈ በጀት የመንግስት መ/ቤቶች የሚያቀርቡትን ሀሳብ መሠረት በመድረግ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ እና እንዲፈቀድ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና ከዚያም ለሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት የሚቀርብ ነው።
- የስራ ዕቅድ ግብአቶችን፣ ውጤቶችን እና የአፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳን የሚያገናኝ የወጪ ማዕከሎች ደጋፊ መረጃ ነው።

## መግቢያ

በኢኮኖሚ በዳበሩ አገሮች የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጠንካራ በመሆኑ መንግሥት በኢኮኖሚዉ ዉስጥ ያለዉ ተሳታፊነት ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች የመንግስት ተሳትፎ ከፍተኛ ሲሆን የመንግስት ፍጆታም ከፍተኛ ነዉ፡፡ መንግስት የሚያስፈልገዉን ገቢና የሚያወጣዉን ወጪም የሚያስተዳድረዉ በበጀት ነዉ፡፡ በመሆኑም በማንኛዉም የመንግስት አስተዳደር ዉስጥ በጀት መጠየቅ፤ በጀት መፍቀድ፤ የተፈቀደዉንም ተግባራዊ አድርጎ ስለ አፈፃፀሙ በየወቅቱ ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ የበጀት ሥርዓት ዋና ተግባር በመሆኑ መንግስት ይህን እዉን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት፡፡

መንግስት የሚያካሂደዉ እንቅስቃሴ ሰፊና ብዙ ሀብት የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ መንግስት በተግባር ሊያዉለዉ የሚችል የፋይናንስ ግኝት መጠን ግን አነስተኛ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት የበጀት ስርዓት የመንግስት ገቢ መጠን ቅድሚያ የሚሰጣዉ የወጪ ዓይነቶች ጋር በማጣጣም ትኩረት የሚሰጣቸዉ ተግባሮች እንዲፈፀሙ ይረዳል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የመንግስት ፖሊሲ ድህነትን መቀነስ ሲሆን ዓላማዉን ለማሣካት የመንግስት ተሳትፎ ብቻዉን በቂ ስላልሆነ የሕዝቡ ተሳትፎ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ሕዝቡና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቅድሚያ የሚሰጡቸዉን ፕሮግራሞች በመጠቆምና ሙስናን በማጋለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሕዝቡም በተገቢዉ መንገድ እንዲሳተፍ ስለበጀት ዝግጅት፤ አፈፃፀምና ቁጥጥር ለህዝብ ግልጽ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ የዚህ ፅሁፍ አላማም በጀት የመንግስትን ፖሊሲ በተለይም በአሁኑ ሰዓት በመካሄድ ላይ ያለዉን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም በማስፈፀም ያለዉን ሚና ግልጽ ማድረግ ነዉ፡፡

የመንግስት የፊሲካል ፖሊሲ የመንደፍና የማስፈፀም ኃላፊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ሲሆን የፊሲካል ፖሊሲ በመንግሥት ገቢ፤ ወጪና የብድር አስተዳደር ላይ ይንፀባረቃል፡፡ ተገቢና ትክክለኛ የፊሲካል ፖሊሲ እንዲኖር ማድረግ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ መረጋጋትና እድገት ወሳኝ ነዉ፡፡ በብዙ አገሮች ተገቢ ያልሆነ የሕዝብ አስተዳደር የድህነት ቅነሳ ዓላማን የሚጎዳ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡
ይህ የበጀት ማንዋል በአስር አርዕስቶች የተከፋፈለ ሲሆን ጽሑፉ የሚጀምረዉ የመንግስት በጀትና የድህነት ቅነሳ ግንኙነትን በአጭሩ በማሳየት ሲሆን በጀት ምን ማለት

እንደሆነም በሁለተኛዉ አርዕስት ተገልፆል፡፡ ሦስተኛዉ አርዕስት የበጀት ሥርዕትን በኢትዮጵያ የሚመለከት ሲሆን አራተኛዉ አርዕስት ደግሞ የበጀት አቋምን በሁለት ንዑስ አርዕስቶች በመከፋፈል ገልፆአል፡፡ በዚህ አርዕስት የመጀመሪያዉ ንዑስ አርዕስት የገቢ በጀት ሲሆን በሥሩ የአገር ዉስጥና የዉጭ ምንጮችን ተመልክቷል፡፡ ሁለተኛዉ ንዑስ አርዕስትም የወጪ በጀትን ይመለከታል፡፡

በመቀጠልም አምስተኛዉና ስድስተኛዉ አርዕስት በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂ መሠረት የበጀት ሥርዕትና አወቃቀር ላይ የተደረጉትን ለዉጦች የሚያስተዋዉቅ ሲሆን በአምስተኛዉ አርዕስት የበጀት ምድብ ምን እንደሚመስል እና በስድስተኛዉ አርዕስት ስለ ዕቅድና በጀት ጊዜ ሠሌዳ ተገልፆል፡፡

በመጨረሻም የመንግስት ሂሳብ አቀራረብና ቁጥጥር፣ የበጀት አስተዳደር ሥርዓት ከሕግ አንፃር፣ ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር በኢትዮጵያ፣ እና የመንግስት ዕቃና አገልግሎት ግዥ እንደቅደም ተከተላቸዉ በሰባተኛ፣ በስምንተኛ ፣ በዘጠነኛና በአስረኛ አርዕስቶች ቀርበዋል፡፡

## 1. የመንግስት በጀትና የድህነት ቅነሳ ግንኙነት

መንግስት ድህነትን ለመቀነስ ከሚጠቀምበት መንገድ አንዱና ዋንኛዉ በጀት ነዉ። በመሆኑም ስለድህነት ቅነሳ በምንነጋገርበት ግዜ በመጀመሪያ ስለበጀት አዘገጃጀት፤ አፈፃፀምና ቁጥጥር ግንዛቤ ማግኘት ለሕዝቡም፤ ለሕግ አዉጭዉም ሆነ ለሕግ አስፈፃሚዉ ጠቃሚ ይሆናል።

ከፍተኛ ዕዳ ያለባቸዉ አገሮች የሚያገኙትን የእዳ ቅነሳና እንዲሁም ከአገር ዉስጥ ምንጭና ከዉጭ ምንጭ የሚያገኙትን አነስተኛ ወለድና የመክፈያ ግዜአቸዉ ረዥም የሆኑትን ብድሮች ለድህነት ቅነሳ የሚያዉሉት በጀትን በመጠቀም ይሆናል። ይህም የሚሆነዉ በመጀመሪያ ለቅነሳ የሚረዱ ሴክተሮችን በመምረጥ፤ የተገኘዉን ገንዘብ ከፍተኛዉን ድርሻ ለእነዚህ ሴክተሮች መመደብና ለእነዚህ ሴክተሮች የተመደበዉ ገንዘብ በትክክል በተግባር መዋሉን ማረጋገጥ ጠቃሚ ይሆናል።

እለም አቀፍ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ድህነትን ለመቀነስ ከተስማሙባቸዉ ዉስጥ

1. እ.ኤ.አ በ2015 በድህነት የሚኖረዉን ሕዝብ በግማሽ መቀነስ፤
2. እ.ኤ.አ በ2015 ሁሉም ልጆች አንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፤
3. በ2005 የፆታ እኩልነትን በማምጣት በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እኩል የሆነ የሴቶችና የወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ማግኘት
4. በ2015 ሁሉም እናቶችና ሕፃናት የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግና፤
5. በ2015 የአካባቢ የተፈጥሮ ሀብትን ከጥፋት ማዳን የሚሉት ይገኙበታል።

እነዚህ አመልካቾች በአገራችንም ትኩረት ተሰጥቶባቸዉ በጊዜያዊ የድህነት ቅነሳ ኘሮግራሙ ተጠቅሰዋል። በኘሮግራሙም ትምህርት፤ ጤና፤ እርሻና መንገድ ትኩረት ያገኙ ሲሆን በ1994 በጀት ሲዘጋጅ ከፍ ያለ ድርሻ እንዲይዙ ተደርጓል።

ማንኛዉም መንግስት ሰፊ የሆነ ፋላጎት ይኖረዋል። ነገር ግን የሕዝብ ሀብት ዉስን በመሆኑ ሁሉንም ፋላጎት ማሟላት አይቻልም። በመሆኑም ድህነትን ለመቀነስ የሚረዱ ሴክተሮችን መምረጥና ከፍተኛዉን ወጪ ለእነዚህ ሴክተሮች መመደብ አስፈላጊ ይሆናል። በጊዜያዊ የድህነት ቅነሳ ኘሮግራሙ ለትምህርት፤ ለጤና፤ ለመንገድ፤

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

ለተፈጥሮ ሀብትና ለግብርና ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለዚህም ተግባራዊነት ዉጤታማ የሆነ የበጀት ሥርዓት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረዉ ይታመናል፡፡ ለምሳሌ በ1994 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት በኩል የሚሰበሰበዉ ገቢ፤ ከዉጭ የሚገኘዉ ብድርና እርዳታ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የመደበኛ የካፒታል ወጪና የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተደግፎ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል፡፡ በበጀት ዓመቱ የፀደቀዉ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ኑሮ እድገት እንዲሁም ድህነትን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብለዉ ለሚታሰቡ የወጪ ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በካፒታል ወጪ በኩልም የመንገድ፤ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፤ የጤናና ትምህርት ወጪዎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸዉ ሲሆን በተለይ የእነዚህ ዘርፎች ወጪ የሚከናወነዉ በክልሎች በኩል በመሆኑ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተመደበዉ የበጀት ድጋፍ ከመነሻዉ ከፍ እንዲል መደረጉ ለድህነት ቅነሳ ኘሮግራም ቀዳሚ ትኩረት መስጠቱን ያመለክታል፡፡

በበጀት አመዳደብ ወቅት ለድህነት ቅነሳ ቅድሚያ መስጠቱ ብቻ ለፖሊሲዉ መሳካት በቂ አይሆንም በመሆኑም ከበጀት ሂደት እስከ አፈፃፀምና ቁጥጥር ድረስ ያለዉን የበጀት ዑር በየጊዜዉ መገምገም ፖሊሲዉን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረዉ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

የሕዝብ ሀብትን ለማደላደል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሁሉም ህብረተሰብ ተሳትፎ የሚያስፈልግ ሲሆን ዋና ዋና ተሳታፊዎች ግን የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

1. የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዉጤታማ የሆነ፤ ከሙስና የፀዳ አገልግሎት ለሕዝብ ማዳረስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መስሪያ ቤቶች የሥራ እቅድ እንዲኖቸዉና ወጪያቸዉም በእቅዳቸዉ መሠረት መሆንና በተሰጣቸዉ የገንዘብ ጣሪያ መሆን ይኖርበታል፡፡ የወጪዎች ክትትል ሥርአት መኖር፤ ሠራተኞች ከድህነት ቅነሳ ኘሮግራሙ ጋር በተየያዘ ያላቸዉ ሥራ አፈፃፀም መበረታታት ይኖርበታል፡፡ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት የድህነት ቅነሣ ኘሮግራሞችን አፈፃፀም መከታተል፤ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት በቁክክር ላይ የተመሠረት መሆን ይኖርበታል ይህም ከግሉ ሴክተር ጋርም

ሊሆን ይችላል። የመንግስት መስሪያ ቤቶችም ተጠያቂነታቸዉ ለሕግ አዉጭዉ ብቻ ሳይሆን ለሕዝብም መሆን ይኖርበታል።

2. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባለበጀት መስሪያ ቤቶች በጀታቸዉን የሚያቀርቡት ከራሳቸዉ ፍላጎት አንፃር ሲሆን የገንዘብና ሚኒስቴርና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የአገሪቱን የገቢ አቅም፣ የመንግስትን የልማት እስትራቴጅ ፣ የድኃነት ቅነሳ ዓላማን በማገናዘብ በጀት ይመድባል። በበጀት አመዳደብ ወቅት ለድህነት ቅነሳ ቅድሚያ በመስጠት መመደብ ብቻ በቂ ስለማይሆን ከበጀት አመዳደብ እስከ አፈፃፀምና ቁጥጥር ድረስ ያለዉን የበጀት ዙር መከታተል አስፈላጊ ይሆናል። በመሆኑም በዉጤት ላይ የተመሠረተ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል። የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ግቡን እንዲመታም በእቅድ የተያዘዉ ሥራ በተግባር በመዋሉ የተገኘዉን ዉጤት በመዳሰስ ይሆናል። ለዚህም ስኬታማነት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጀታቸዉን በሚጠይቁበት ጊዜ የሥራ እቅዳቸዉንና የዉጤት አመልካቾቻቸዉን አብረዉ እንዲያቀርቡ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። የተደረጉ ወጪዎች ከተከናወኑ የፊዚካል ሥራዎች ጋርና ከእቅዱ ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል።

3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በበጀት ጉዳይ ላይ ከሚያከናዉኗቸዉ ተግባሮች ዉስጥ የሕዝብ አስተዳደር ዉጤታማ መሆኑን መቆጣጠር፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ፍላጎት ቅድሚያ ከሚሰጣቸዉ ፕ ሮግራሞች ጋር ማጣጣም፣ የሕዝብን ፍላጎት በበጀት እንዲተገበር ማድረግ እና በጀቱን ወደሕግ መቀየር የሚሉት ይገኙበታል።

ትክክለኛ በጀት ለማዘጋጀትም የሚቻለዉ በቅድሚያ የኢኮኖሚ እድገትን እና በወቅቱ ያለዉን ሀብት በትክክል መገመት ሲቻል ሲሆን ትክክለኛ ያልሆነ ግምት ግን የመንግስት ፖሊሲ እንዳይተገበር ያደርጋል። በመሆኑም የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ግዜ እቅድ አስፈላጊ ይሆናል። ዓመታዊ በጀትም ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለማስተካከል፣ በዓመቱ ቅድሚያ የተሰጣቸዉን ፕሮግራሞች ለማካተትና ካለፈዉ ስህተት ለመማር ይረዳል።

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

በአጠቃላይ ዉስን የሆነዉን የሕዝብ ሀብት በተገቢዉ መንገድ፣ ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉና ለድህነት ቅነሳ ለመጠቀም የሚከተሉትን መንገዶች መከተል ጠቃሚ ይሆናል፡፡

1. በረዥም፣ በመካከለኛ፣ እና በዓመታዊ የግዜ ዕቅድ መጠቀም /በጀት የዕቅድ ማስፈፀሚያ መሣሪያ ነዉ፡፡ በመሆኑም የመንግስትን ፖሊሲ የድህነት ቅነሳ ፕ ሮግራምን ጨምሮ ለመተግበር ዓመታዊ የበጀት ሂደት ዋና መሳሪያ ይሆናል፡፡
2. ገቢንና ወጪን በትክክለኛዉ መንገድ ማቀድ
3. በወቅቱ በጀት ማወጅና በህጉ መሠረት ወጪ መፈፀም
4. ገንዘብ ሚኒስቴር ለሕዝብ ተወካዩች በወቅቱና በትክክለኛዉ የመንግስትን ገቢና ወጪን ከእቅዱ ጋር በማገናዘብ ሪፖርት ማድረግ
5. ዋና ኦዲተርም በጀት በትክክል በሥራ መተርጎሙን ሪፖርት ማድረግና ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ
6. የሂሳብ አያያዝን፣ ቁጥጥርን፣ እና የግዥ ተግባርን ማሻሻል
7. ለዋጋ ትኩረት መስጠት
8. ለሁሉም የወጪ ዓይነቶች ተገቢዉን ትኩረት መስጠት
9. የበጀት ቀመርን /formula/ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል
10. የዉጭ እርዳታና በጀትን ማገናኘት እና
11. ግልጽነት /transparency/ ናቸዉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጠቃሚ ነጥቦች ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የሕዝብ ሀብት አስተዳደርን ለማሻሻል በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ስር በሚገኘዉ የበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂ ሁሉን አቀፍ የሆነ መጠነ ሰፊ የማሻሻያ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነዉ፡፡ ይህ የበጀት ማሻሻያ ጥናት ሁለት ለዉጦችን የሚያካትት ሲሆን እነዚህም የበጀት ሥርዓት እና አወቃቀር ለዉጦች ናቸዉ፡፡ የበጀት ሥርዓት የበጀት ዝግጅትን እና አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የበጀት አወቃቀር የበጀት መረጃዎች በቅጽ የሚደራጁበት ዘዴ ነዉ፡፡ የበጀት የጊዜ ሠሌዳ በበጀት ዝግጅት ሂደት ዉስጥ ሊከናወኑ የሚገባቸዉን ተግባሮች የሚያሳይ የበጀት ሥርዓት አንድ ምሳሌ ነዉ፡፡ የመንግሥት የሂሣብ አወቃቀር ሥርዓት የበጀት መረጃ እንዴት እንደሚደራጅ የሚያሳይ የበጀት አወቃቀር አንድ ምሳሌ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ገቢን ለማሳደግ ትኩረት ከተሰጠዉ አንዱ ሲሆን በሚወሰዱ የታክስ ፖሊሲዎች እና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎችም የመንግስት ገቢ እንደሚጨምርም ይገመታል፡፡

## 2. በጀት ምንድን ነዉ

ኅብረተሰብ ያለመንግስት አይታሰብም መንግስትም ያለበጀት አይኖርም፡፡ የአንድ መንግስት አንደኛ ተግባሩ ሕግን ማስከበር እና ጸጥታን መስጠት ነዉ፡፡ መንግስትና በጀት ሊኖሩ ያስፈለገበት ዋንኛዉ ምክንያት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያቀርባቸዉ የማይችላቸዉ የጋራ መገልገያዎች /social goods/ መፈጠር ነዉ፡፡ በጀት የአንድ መንግስት አመታዊ ተግባራት መታያ ነዉ፡፡ በጀት በአንድ የእቅድ ዘመን መንግስት የሚኖረዉን ገቢና ወጪ የሚያመለክት ትንቢያ ነዉ፡፡ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት የበጀት ቃል አመጣጡ ቡዠት /Bougette/ ከሚል የፈረንሳይኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ትንሿ ቦርሳ ማለት ነዉ፡፡

በጀት ማለት የመንግስት ገቢና ለየመ/ቤቱ የሚተላለፍ የገንዘብ ድርሻ ነዉ፡፡ በጀት የአንድ አገር የግብር፣ የብድር፣ የእርዳታ እና የወጪ ሰነድ ሲሆን የመንግስት ፊስካል ሞኒተሪ ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም የሚያስችል መሳሪያ ነዉ፡፡ ባጠቃላይ በጀት ለአንድ መንግስት ማንነት ጥሩ መለኪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ የገቢ መሰረትን በማስፋትና በወጪዉ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ የምንጠቀምበት የእድገት ቁልፍ መሳሪያም ነዉ፡፡ በመሆኑም መንግስት ሕግን፣ ሥርዓትን የማስከበር፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ሊያመጡ የሚችሉ የመሠረተ ልማት አዉታሮችን የመዘርጋት እንዲሁም ማህበራዊ ደህንነት የማረጋገጥ ኀላፊነቱን በብቃት ለመወጣት እንዲችል የግብር አዋጆችን እና የበጀት አዋጆችን በየጊዜዉ እያወጣ ያስፈጽማል፡፡

### 2.1 የበጀት አስፈላጊነት

በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን በጀት በቀላሉ ገቢን ለማመንጨት እና የመንግስት ወጪን ለመሸፈን ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዋና መሳሪያም ሆኗል፡፡ ተገቢ የሆነ የገቢና የወጪ በጀት ማስተዳደር ለብሄራዊ ኢኮኖሚ መዳበር አስተዋፀኦ አለዉ፡፡ እንደ አገሮች የእድገት ደረጃ ይለያይ እንጂ የግል ክፍለ ኢኮኖሚዎች ሊሸፍኗቸዉ የማይችሉአቸዉ ግልጋሎቶች በሁሉም ሀገር ይኖራሉ፡፡ በአንድ ህብረተሰብ ዉስጥ በማህበር የሚፈለጉ ግልጋሎቶች ነገር ግን በግል ሊሸፈኑ የማይችሉ እንደ አገር መከላከልና የፍትህ ሥራ የመሳሰሉትን ለማከናወን እና የህዝብ ዉስን ሀብትም ከሚኖረዉ ሰፊ ፍላጎት ጋር አለመጣጣም የተነሣ በህዝብ ሀብት አስተዳደር /public finance/ሥርዓት ዉስጥ ዓይነተኛ ሚና የሚጫወት በጀት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ በጀት የእቅድ ማስፈፀሚያ መሣሪያና

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም ከመሆኑም በላይ የሀብት አጠቃቀምን በመወሰን ቁልፍ የልማት ፖሊሲ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል።

በጀት በረጅም (በመካከለኛ) እና በዓመታዊ እቅዶች የተዘረዘሩትን የመንግሥት ፕሮግራሞች በሥራ ለመተርጎም የሚጠቅም ነዉ። በአንድ አገር የተወሰነዉን የሕዝብ ሀብት ወሰን ከሌለዉ የሕዝብ ፍላጎት ጋር ማጣጣም አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። ይህንንም ለማድረግ የፍላጎቶችን ቅደም ተከተል ማጥናትና ማወቅ አስፈላጊ ነዉ። ስለ አንድ ሃገር የኢኮኖሚና የሶሻል እድገት የሚያገለግሉ የፊስካልና የሞኒተሪ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በጀት ዋና መሳሪያ ነዉ።

በጀት በታክስ መሠረት ገቢን ለሕብረተሰቡ የሚያከፋፍል ሲሆን መንግስት የተጎዱ ክልሎችን ከሌሎች እኩል ለማድረግም የሚጠቀምበት መሣሪያ ነዉ። የጋራ መገልገያዎች /Public goods/ የምንላቸዉ ምርቶች ነፃ ተጠቃሚዎች/free riders/ ይዞ የሚሄድ ስለሆነ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የዚህ ዓይነት ግልጋሎቶችን ሊሰጥ አይችልም። በመሆኑም እነዚህን ግልጋሎቶች ዉጤታማና ስኬታማ በሆነ መንገድ ለሕዝብ ማቅረብና ብሔራዊ የሀብት ክፍፍሉም ኢኮኖሚያዊና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነዉ። ጊዜ የማይሰጡና ለእድገትም መሰረት የሆኑ ተግባራት ታዉቀዉ በቅደም ተከተል መቀመጥ ይኖርባቸዋል። የዚህ ዓይነቱ የሀብት ድልድል ለሁሉም ሕብረተሰብ እኩል ነዉ። ምክንያቱም አገልግሎቱ ለአንድ ተጠቃሚ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ለምሳሌ ለጎዳና መብራቶች ግብር የከፈለም ያልከፈለም እኩል ተጠቃሚ ነዉ። ስለሆነም ትኩረቱ በማህበረሰብ ብልፅግና/welfare/ ስለሚሆን ያልከፈለን ወገን ማግለል አይቻልም። በብሔራዊ ሀብት ድልድል ጊዜ የመንግስት በጀት ፊስካልና ሞኒተሪ ፖሊሲዎችን በማስፈጸም የሚፈለገዉን እድገት በማስገኘት አስተዋጽኦ አለዉ። የመንግስት የሀብት አመዳደብ በፍላጎት ቅደም ተከተል /priority/ መሆን አለበት። እነዚህ ቅደም ተከተል የሚመለከቱት ደግሞ ለአጠቃላይ ሕብረተሰቡ በምርታማነት እና በእኩልነት መስኮች ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ እየተመዘኑ ይሆናል።

የመንግስት በጀት በተለየየ መንገድ የአንድ ሃገር ኢኮኖሚን ሊያረጋጋ ይችላል። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማረጋጋት መንግሥት በሁለት አብይ ፖሊሲዎች ይጠቀማል። እነርሱም ፊሲካል እና ሞኒተሪ ፖሊሲ ናቸዉ። የገንዘብ ፖሊሲዎችን/monetary policy/

በመጠቀም ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ይቻላል:: የባንክ ወለድን መቀነስ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ሲሆን ቁጠባን ግን አያበረታታም:: በሌላ መንገድ የባንክ ወለድን መጨመር ኢንቨስትመንትን የሚያዳክም ሲሆን ቁጠባን ግን ያበረታታል:: በተጨማሪም ወደ ኢኮኖሚዉ የሚገባዉን ገንዘብ በመቆጣጠር፤ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፤ የግብር ደንቦችን በመለዋወጥ ኢኮኖሚዉን ማረጋጋት ይቻላል:: ለምሳሌ መንግስት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ቦንድን እንደመሳሪያነት ይጠቀምበታል::

## 3. የበጀት ሥርዓት በኢትዮጵያ

በጀት በኢትዮጵያ ከመንግስት አስተዳደር እድገት ደረጃ ጋር ተያይዞ ተግባራዊ እየሆነ መምጣቱን የታሪካ መረጃዎች ያስረዳሉ:: በጀት እንደ ሥርዓት ሕግ/ደንብ ሆኖ የታወቀዉ በአፄ ምኒሊክ ዘመን ሲሆን በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣዉ ግን በ1936 ዓ.ም ነበር:: ከ1938 ዓ.ም በኋላም በነጋሪት ጋዜጣ ሳይወጣ ለ7 ዓመት ቆይቶ በ1945 ዓ.ም እንደገንዘብ ሚኒስቴር ማስታወቂያ ሆኖ ወጥቷል:: በ1948 በተሻሻለዉ ሕገ መንግስትም በጀት ለፋናንስ አስተዳደር መቆጣጠሪያ መሣሪያ መሆኑ በመታወቁ በምእራፍ 7 ላይ መሠረታዊ ሕጎች ሰፍረዋል:: እነርሱም

- በሕግ ካልሆነ በቀር ታክስ፣ ቀረጥ፣ ግብር፤ ኤክሳይዝ ቀረጥ አይጣልም፤ አይጨመርም፤ አይቀነስም፤ ወይም አይፋቅም፤ በሕግ ካልተፈቀደ በቀር በሕግ የተወሰነዉን ማናቸዉንም ታክስ፣ ቀረጥ፤ ግብር ወይም ኤክሳይዝ ቀረጥ ከመክፈል የሚያስቀር ነገር የለም:: /አንቀጽ 113/
- የበጀት ዓመት በልዩ ሕግ ይወሰናል:: በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድና ሕግ በሚፈቅደዉ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለመጪዉ ዓመት በሥራ ላይ የሚዉለዉ በጀት የሚፈቀድበትን በጀት አሳብ ጨምሮ የሕግ አሳብ እያሰናዳ በየመቱ ለፓርላሜንቱ ያቀርባል:: /አንቀጽ 114/
- ፓርላሜንቱ የቀረበለትን በጀት በዝርዝር መርምሮ አንድ በአንድ ድምጽ ይሰጥበታል:: ስለወጪ በበጀቱ ከተመለከተዉ ከጠቅላላዉ ገንዘብ በላይ ፓርላሜንቱ በማናቸዉም አይነት መጨመር አይችልም:: ... ፓርላሜንቱ በበጀቱ ላይ ድምጽ መስጠቱን እጅግ ቢያንስ አዲሱ የበጀት ዓመት ከሚጀመርበት ካንድ ወር በፊት መጨረስ አለበት:: /አንቀጽ 116/

እያንዳንዱ የበጀት ዓመት በተፈፀመ በአራት ወር ዉስጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዚያዉኑ የተፈፀመዉን ዓመት የገቢና የወጪ ሙሉ ሪፖርት ለንጉሠ ነገሥቱና

ለፓርላማ ያቀርባል፡፡ ሪፖርቱም ወዲያዉኑ ለዋናዉ ኦዲተር ይላካል፡፡ ኦዲተሩም በሪፖርት ላይ ያለዉን አስተያየት በሶስት ወር ዉስጥ ለንጉሠ ነገሥቱና ለፓርላሜንቱ ያቀርባል፡፡ /አንቀጽ 120/ የሚል ሲሆን በጀት ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ ሥርአቱን በመጠበቅ በፓርላማዉ እየፀደቀ በሕግ ሲወጣ ቆይቷል፡፡ በደርግ ዘመን መንግሥትም በአመታዊ የበጀት አዋጅ ብቻ የመንግስት ወጪ ሲመራ ቆይቷል፡፡

## 4. የበጀት አቋም

ከሂሣብ አያያዝና አወቃቀር ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ የበጀት አቀማመጥ የገቢና የወጪ ተብሎ ይመደባል፡፡ ስለሆነም በጀት ገቢና ወጪ ተብሎ የሚከፈል ሲሆን በጀት ሲዘጋጅ የገቢ በጀትንና የወጪ ዕቅድን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዝግጅት ጊዜ በሕዝብ የሚጠበቁ አገልግሎቶች፤ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገዉ ወጪና ወጪዉ የሚሸፈንበት ምንጭ ይታሰባል፡፡

### 4.1 የገቢ በጀት

መንግስት ዓላማዉን ለማሳካት ወጪ ያስፈልገዋል፡፡ ይህንንም ለማሳካት የመንግስት የማስገበር ሥልጣንና የሕዝብ የመገበር ግዴታ መፈጠሩን እና አመጣጡም ከሕዝብ ፈቃደኝነት ሳይሆን ከጦርነት ማሽነሪ ጋር የተያያዘ እንደነበር የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ የግብር ግዴታና የመንግስት ጠቀሜታ የኋላ ኋላ ሕዝብ እያመነበት የመጣ ሲሆን ግብር መክፈል የተጀመረዉም በጉልበትና ከምርቱ የተወሰነ ድርሻ በመስጠት ነበር፡፡ መንግስት ሁለት ዓይነት የገቢ ምንጮች ያሉት ሲሆን እነሱም የሃገር ዉስጥና የዉጭ ሃገር ምንጮች ናቸዉ፡፡

#### 4.1.1 የሃገር ዉስጥ የገቢ ምንጮች

የመንግስት የሃገር ዉስጥ የገቢ ምንጮች ታክስ፤ ታክስ ያልሆኑ እና ካፒታል ናቸዉ፡፡ በበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂዉ መሠረት የአገር ዉስጥ ገቢ ዓይነቶች ለፌዴራል እና ለክልል መንግሥታት የሚያገለግል ተመሳሳይ የገቢ መለያ ቁጥር እንዲኖራቸዉ እና የዐለም ዐቀፍ የገንዘብ ድርጅት የመንግስት የፋይናንስ እስታቲስቲክስ የገቢ ምድቦችን እንዲከተል ተደርጓል፡፡ የገቢ መለያ ቁጥሮች ለሁሉም መንግሥታት አንድ ዓይነት

እንዲሆኑ ማድረግ ለገቢ ትንበያ ፤ ለብሄራዊ እና ክልላዊ ሂሣብ ዝግጅት ተመሳሳይ በሆነ የበጀት እና የሂሣብ የኮምፒዉተር አሠራር ለመጠቀም ያግዛል:: ስለሆነም የፌደራል፣ የክልል መንግስታት ወይም የአስተዳደር ምክር ቤቶች ታክስ ቢጥሉ ይህ ታክስ ተመሳሳይ የሆነዉ የአገር ዉስጥ ገቢ መለያ ቁጥር ይሰጠዋል ማለት ነዉ:: ለምሳሌ በኪራይ ገቢ ላይ ለሚከፈል ግብር የተሰጠዉ 1102 የመለያ ቁጥር ለፌደራል እና ለክልል መንግሥታት እንዲሁም ለመስተዳድር ምክር ቤቶች ያገለግላሉ::/ዝርዝሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ /

#### 4.1.1.1 የታክስ ገቢ

የግብር ታክስ ከመንግስት አመሠራረት ጋር አብሮ የመጣ ቢሆንም ግብር ተብለዉ ሊጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት ግዴታዎች በ15ኛዉ ክፍለ ዘመን እንደነበሩ አንዳንድ የጽሁፍ ማስረጃዎች ያመለክታሉ:: ሆኖም በዓይነት ወይም በአገልግሎት ይከፈል የነበረ ግብር ሥርዓት እየያዘ የመጣበት ወቅት ከ19ኛዉ ክፍለ ዘመን ወዲህ ነዉ:: በ19ኛዉ ክፍለ ዘመን ማብቅያና በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ግብርን የመጣልና የግብርን አሠባሰብ ሥርአትን የመዘርጋቱ ጉዳይ ተቀባይነትን እያገኘ በመምጣቱ የመንግሥትን የገንዘብ አቅም ለማጠናከር ከገቢ ላይ ግብርን የመሰብሰብ ሥራ እንደተጀመረ መረጃዎች ያስረዳሉ:: አገሮች ዘመናዊ ነዉ የሚባለዉን የታክስ ዓይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያስተዋዉቁ የመጡ ሲሆን ከዚህም መካከል የእንግሊዝ 1907፣ የአሜሪካ 1913፤ የፈረንሳይ 1917 /እ.ኤ.አ/ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸዉ:: በኢትዮጵያም እንደምንገኘዉም አገር ከጥንታዊ የግብር አሰባሰብ ዘዴ የተጀመረዉ ግብር ዛሬ የአሰባሰብ ሥርዐቱንና የግብር አይነቶችን በዘመናዊ መልክ በማደራጀት አዲስ መልክ ይዞ ይገኛል::

ከማናቸዉም ገቢ ግብር ስለማስከፈል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 173/53 እና በየጊዜዉ በወጡ የታክስ አዋጆች መሠረት በፌደራል መንግሥት እንዲሰበሰቡ የተመደቡትን ግብሮችና ልዩ ልዩ ታክሶች በየዓመቱ የመወሰን፤ የመሰብሰብ፤ በአግባቡ መዝግቦ ለመንግስት ገቢ የማድረግና የማሳወቅ ሀላፊነት የአገር ዉስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነዉ::

ግብር ለመንግስት ገቢ የማስገኘት ጠቀሜታ ያለዉ ሲሆን የግብር አጣጣሉም የሚከተሉትን መርሆዎች ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል::

1. የታክስ ገቢ የማስገኘት ብቃት
2. በታክስ ከፋዩ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመከላከል

3 በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሉች ወደ ጎን ወይም ወደታች እና ወደ ላይ በሚገኙ እርከኖች በአኩልነት የመፈፀም ብቃት

4 የኢንቨስትመን እንቅስቃሴዎችን የማያዳክምና የማይገድብ

5 ግልጽ የሆኑ የግብር ህጎች እና ብቃት ያለዉ የታክስ አስተዳደር መኖር ናቸዉ።

የታክስ ገቢዎች ለመንግስት በሕግ የተወሰኑ ክፍያዎች ናቸዉ። የመንግስት የገቢ ምንጭ አንዱና ዋነኛዉ ታክስ በመሆኑ የሚሰራበት የታክስ ሕግ ገቢን ከማመንጨት ባሻገር የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የመስራት ፍላጎትና የኢንቨስትመንትን ዉሳኔ የሚያበረታታ መሆን አለበት። የታክስ ፖሊሲንም ሆነ የታክስ አስተዳደርን ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎች የመጨረሻ ግብ የመንግስትን ገቢ የማሳደግና አንዳንድ ፖሊሲዎች ማስፈጸም ነዉ። ለዚህም የገቢ መሰረትን ማስፋት፣ የታክስ ከፋዩን ፈቃደኝነትና የታክስ ሰብሳቢዉን የማስፈጸም ብቃት ማጎልበት እና ለገቢ ሰብሳቢ የሚረዱ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ማዉጣት ተቀዳሚ ተግባር ነዉ።

በታክስ ስር ዘጠኝ ንዑስ ክፍሎች አሉ። እነሱም

1. በገቢ፣ በትርፍ እና በካፒታል ዋጋ እድገት በተገኘ ጥቅም ላይ የሚከፈል ታክስ
2. በሃገር ዉስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ
3. በሃገር ዉስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የሽያጭ ታክስ
4. የአገልግሎት ሽያጭ ታክስ
5. የቴምብር ሽያጭ እና ቀረጥ
6. ወደ ሃገር ዉስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የጉምሩክ ቀረጥ
7. ወደ ሃገር ዉስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ
8. ወደ ሃገር ዉስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የሽያጭ ታክስ
9. ወደ ዉጭ በሚላኩ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ታክስ ናቸዉ።

ከሰዎችና ከስራዎች ሁሉ ግብር እንዲከፈል የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 60/1936 ከመስከረም 1 ቀን 1936 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ተወስኗል። ከዚያ ወዲህ አዋጅ ቁጥር 60/1936ን ያሻሻለዉ በ1941 ዓ.ም የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 107/1941 ነበር። በዚህ አዋጅ

መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ የተወሰደዉ ማናቸዉም ዓይነትና በማናቸዉም ዓይነት የተገኘ ትርፍ፤ ጥቅም የቤት ኪራይ ፤ደመወዝ፤ የሙያ ወይም የአገልግሎት ዋጋን እና በድካም ወይም ያለድካም የተገኘ ማንኛዉም ዓይነት ገቢን ይጨምራል።

ከላይ የተመለከተዉ አዋጅ መሠረታዊ የግብር አጣጣል ፤ አወሳሰን እና አሰባሰብ ሥርዓት የተከተለ ቢሆንም ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በመጀመሪያ አዋጅ ቁጥር 19/1949 ቢወጣም የተሻሻለ አዋጅ በማስፈለጉ ከማናቸዉም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የሚያስችል አዋጅ ቁጥር 173/1953 በተግባር እንዲዉል ተደረገ። ይህንኑ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል እና ከዚያ ወዲህም የተለያዩ የገቢ ግብር ሕጎች ወጥተዉ በሥራ ላይ በመዋል ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ መንግስት ለሚያከናዉናቸዉ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገዉን ወጪ ለመሸፈን ገቢ ከሚያገኝባቸዉ ወይም ከሚሰበስባቸዉ ምንጮች አንዱ ከአገር ዉስጥ የሚሰበሰብ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርና ታክስ ነዉ። ቀጥተኛ የሆኑ ታክሶችን ለማስተዳደር አዋጅ ቁጥር 173/1953 /እንደተሻሻለዉ/ ፤ደንብ ቁጥር 258/1955፤ አዋጅ ቁጥር 62/1985፤ 108/1987 እንዲሁም ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን ለማስተዳደር አዋጅ ቁጥር 68/1985፤77/1989 /ማሻሻያ/ ፤ 149/1991 /ማሻሻያ/ እና አዋጅ ቁጥር 110/1991 በዋናነት የሚጠቀሱ የግብር ህጎች/ደንቦች ናቸዉ።

ቀጥታ ታክሶች በአዋጅ የተጣሉ እና በገቢ ላይ የተመሠረቱ ናቸዉ። ቀጥታ ታክስ ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ድርጅት ከሚያገኘዉ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ሲሆን ታክሱ በማንኛዉም መስክ በተገኘ ገቢ ላይ በቀጥታ የሚጣል ነዉ። በሀገራችን የታክስ መዋቅር ዉስጥ ቀጥታ ታክሶች ከምንጻና ደመወዝ፤ ከኪራይ ገቢ፤ ከግለሰብ ነጋዴዎች ከሚያገኙት ትርፍ፤ የንግድ ድርጅቶች ትርፍ፤ ከአክስዮን ድርሻ እና ከእድል መክፈ የሚገኝ ገቢ፤ ከካፒታል ዋጋ እድገት ከሚገኝ ጥቅም፤ ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር፤ ከሮያሊቲ ይሰበሰባል። /አባሪ አንድ/

ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች በማምረቻ ዋጋ፤ በምርትና አገልገሎት መሸጫ ዋጋ ላይ የሚከፈሉ /የሚሰበሰቡ/ ታክሶች ናቸዉ። ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ኤክሳይዝና ሽያጭ ተብለዉ ሲለዩ እነዚህ ታክሶች በሌላ አገላለጽ የፍጆታ ታክሶች በመባል የሚታወቁ ናቸዉ። በተጨማሪም የቴምብር ቀረጥ /ሽያጭ/ በዚህ ምድብ ዉስጥ የምንመለከታቸዉ ይሆናሉ።

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

የሽያጭ ታክስ በምርትና አገልግሎት ላይ የተጣለ ሲሆን በአገር ዉስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ በአምራቾች ደረጃ የሚሰበሰብ ነዉ። በአገር ዉስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የተጣለዉ ታክስ በትምህርት፣ ጤና፣ ዉሃና መብራት ላይ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በስተቀር በሌሎች ላይ እንዲከፈሉ ተደርጓል።

- የሽያጭ ታክስ ስሌት መሠረቱ
- በአገር ዉስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ የአምራቹ የጅምላ መሸጫ ዋጋ፣ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ የተከፈለዉ የኤክሳይዝ ታክስ ድምር፣
- ወደ አገር ዉስጥ ለሚገቡ ዕቃዎች የዕቃዉን ዋጋ የመድንና የማስጫኛ ክፍያ/ሲ.አይ.ኤፍ./ ፣እንዲሁም የጉምሩክ ቀረጥና እንደ አግባብነቱ የተከፈለዉ የኤክሣይዝ ታክስ ድምር፤ እና
- ለአገልግሎቶች የአገልግሎት መሸጫ ዋጋ ይሆናል።

የአገልግሎት ሽያጭ ታክስ የሚከፈልባቸዉ የሥራ ዘርፎች

1. ቴሌኮሙኒኬሽን
2. ጋራዥ
3. ልብስ ንጽሕና መስጫ
4. የልብስ ስፌት
5. ጥብቅና
6. የትርጉም ሥራ
7. ሲኒማ ቤት
8. ፀጉር ማስተካከል እና የቁንጅና ሳሉን ሥራ
9. ቴረስት ማስተናገድ
10. ዕቃ ማከራየት
11. ፎቶግራፍና ፎቶ ኮፒ ማንሣት
12. ሂሣብ ምርመራ
13. ሥራ ተቋራጭ
14. መኝታ ቤት
15. አማካሪነት
16. ኮሚሽን ኤጀንት
17. የሂሣብ ሥራ አገልግሎት
18. ፋይናንስ አገልግሎት
19. ተባይ ማጥፊያ
20. ማስታወቂያ

በኤክሳይዝና ሽያጭ ታክስ አዋጅ ቁጥር 68/85 እና ቀጥሎም በአዋጅ ቁጥሮች 77/89 እና 149/91 እንደተሻሻለዉ በአገር ዉስጥ የሚመረቱም ሆነ ከዉጭ አገር የሚመጡ ተመሣሣይ ምርቶች በተመሣሣይ የታክስ መጣኔ /5 ወይም 12 ፐርሰንት/ ታክሱ ይከፈልባቸዋል። ይህ አዋጅ እንደገና ተሻሽሎ 12 በመቶ የሽያጭ ታክስ ይከፈልባቸዉ የነበሩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ወደ 15 በመቶ ከፍ እንዲል ተደርጓል። በአጠቃላይ

በአገር ውስጥ በሚመረተው ላይ ታክሱ የሚከፈለው በአምራቹ ሲሆን ከውጭ በሚመጣው ላይ በአስመጭው ነው፡፡ የክፍያውም ጊዜ በአገር ውስጥ በሚመረተው ላይ ሽያጭ ከተከናወነበት ወር ቀጥሎ በአለው ወር ሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ነው፡፡ የአገልግሎት ሽያጭ ታክስ የሚከፈለው በአገልግሎቶች ላይ ሲሆን የታክሱ መሠረትም የአገልግሎት የመሸጫ ዋጋ ነው፡፡ የመክፈያ ጊዜውም አገልግሎት ከተሰጠበት ወር ቀጥሎ በአለው ወር በአሉት ሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ነው፡፡
የኤክሳይዝ ታክስ ሰፊ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ከሌላቸው ምርቶች፣ የቅንጦት እቃዎች፣ የተሻለ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚጠቀሙባቸው የፍጆታ እቃዎች የበለጠ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ ታክስ የሚታቀፉት ዋና ዋና ምርቶች አልኮል፣ ትምባሆ፣ ሽቶ፣ ስኳር፣ ለስላሳ መጠጥና የማዕድን ውሃ ናቸው፡፡

የቴምብር ሽያጭ እና ቀረጥ እንደባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ፣ የውክልና ሥልጣን፣ የፊርማ ማረጋገጫ ወዘተ. ባሉ ሰነዶች እንዲሁም ለፍ/ቤት የሚያገለግሉ እንደ ውሎች ወይም ሰነዶች ያሉና ሕግ በሚያዘው መሠረት ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የሕግ ሰነዶች ላይ የሚለጠፈውን ቴምብር ሽያጭ የሚመለከት ነው፡፡

ታክስ የኢኮኖሚን እንቅስቃሴና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መሆን ያለበት ሲሆን ዋና ዓላማው ግን ለመንግስት የገቢ ምንጭ ማግኛ መንገድ ነው፡፡ ከ1983 ዓ.ም በፊት መንግስት ታክስን እንደ ገቢ ማስገኛ እና አኩለነትን ለማስፈን ይጠቀምበት ስለነበር የገቢ ግብር እስከ 89 ፐርሰንት ደርሶ የነበር ሲሆን የተቀምሩክ ቀረጥም እስከ 230 ፐርሰንት ደርሶ ነበር፡፡ በታዳጊ አገሮች ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በኢትዮጵያም ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች 60 ፐርሰንት በላይ የሚይዙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የውጭ ንግድ ታክስ 40 ፐርሰንት ይሆናል፡፡ / ሠንጠረዥ 1/፡፡

ሠንጠረዥ 1

የታክስ ገቢ 1983 - 1992 / በፐርሰንት/

| የገቢ ዓይነቶች | 1983 | 1984 | 1985 | 1986 | 1987 | 1988 | 1989 | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቀጥተኛ ታክስ | 40.5 | 41.0 | 33.4 | 30.7 | 33.8 | 37.1 | 35.6 | 35.5 | 35.9 | 36.1 |
| ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ | 59.5 | 59.0 | 66.6 | 69.3 | 66.2 | 62.9 | 64.4 | 64.5 | 64.1 | 63.9 |
| የአገር ዉስጥ ንግድ | 36.9 | 33.0 | 33.8 | 27.1 | 24.4 | 24.5 | 24.1 | 22.4 | 21.5 | 22.4 |
| የዉጭ ንግድ ታክስ | 22.6 | 26.0 | 32.7 | 42.2 | 41.8 | 38.4 | 40.4 | 42.1 | 42.5 | 41.5 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

#### 4.1.1.2 ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች

ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች የመንግሥት ገቢ ሁለተኛ ክፍል ነዉ፡፡ ይህ የመንግሥት ገቢ ክፍል ከካፒታል ሽያጭ በስተቀር ማናቸዉንም የመንግሥት ገቢ፣ የግብር ግዴታን ባለመወጣት ከሚጣል መቀጫ በስተቀር ማናቸዉንም ሌላ መቀጫ እና በመንግሥት ባለቤትነት ስር ከሚገኙ የፋይናንስ ምንጮች በስተቀር በፈቃደኝነት ለመንግሥት ገቢ የሚደረገዉን ማናቸዉንም ገንዘብ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ይህ የመንግሥት ገቢ ክፍል ከታክስ፣ ከእርዳታ፣ ከብድር፣ ከቋሚ ንብረት ሽያጭ፣ በመጋዘን ከሚገኙ እቃዎች፣ ግዑዛዊ ህልዉት ከሌላቸዉ ንብረቶች ሽያጭ እና ለካፒታል ንብረት ማፍሪያ እንዲዉል በመንግሥት ስር ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኘዉን ስጦታ አይጨምርም፡፡

1. በአጠቃላይ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች የሚያጠቃልላቸዉ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡
2. የአስተዳደር ክፍያዎች
3. የመንግስት እቃና አገልግሎት ሽያጭ
4. ከመንግስት ኢንቨስትመንት የሚገኝ ገቢ
5. መደበኛ ያልሆኑ እና ልዩ ልዩ ገቢ እና
6. ለጡረታ ፈንድ መዋጮ ናቸዉ፡፡

#### 4.1.1.3 ከካፒታል የሚገኝ ገቢ

የካፒታል ገቢ ከሚከተሉት ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ይጨምራል። የመኖሪያ ህንፃዎች፣ መኖሪያ ያልሆኑ ህንፃዎች፣ ሌሎች ግንባታዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽኖች፣ ሌሎች መሣሪያዎች፣ በመጋዘን የሚገኙ እቃዎች ሽያጭ፣ ግዑዛዊ ሀልወት የሌላቸው ንብረቶች ሽያጭ፣ እንዲሁም የካፒታል ንብረት ለማፍራት እንዲውል የመንግሥት ካልሆኑ ምንጮች የሚገኝ እርዳታ ናቸው።

ሠንጠረዥ 2

የክልሎች እና የፌዴራል መንግሥት ጠቅላላ ገቢ /በሚልዮን ብር/

| ዓ.ም/ክልል | 1986 | 1987 | 1988 | 1989 | 1990 | 1991 | 1992 | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 44.22 | 58.53 | 86.22 | 104.98 | 95.35 | 81.31 | 82.39 | 79 |
| አፋር | 7.11 | 9.74 | 11.1 | 14.69 | 13.79 | 9.77 | 12.01 | 11.17 |
| አማራ | 95.03 | 120.42 | 135.22 | 160.12 | 180.69 | 188.44 | 193.27 | 153.31 |
| ኦሮሚያ | 215.32 | 248.87 | 331.65 | 378.04 | 386.86 | 375.59 | 446.45 | 340.4 |
| ሶማሌ | 43.36 | 47.11 | 40.03 | 39.13 | 33.32 | 25.49 | 38.84 | 38.183 |
| ቤንሻንጉል | 3.59 | 5.04 | 5.47 | 6.88 | 8.58 | 9.4 | 15.62 | 7.797 |
| ደ.ብ.ብ.ሕ | 72.33 | 104.86 | 143.43 | 157.57 | 164.4[illegible] | 154.72 | 169.95 | 138.2 |
| ጋምቤላ | 3.95 | 5.43 | 4.9 | 7.23 | 7.01 | 7.54 | 7.8 | 6.266 |
| ሐረር | 5.72 | 5.93 | 7.74 | 7.72 | 8.36 | 10.16 | 9.59 | 7.89 |
| አ.አ | 184.68 | 262.26 | 348.77 | 463.28 | 682.01 | 669.89 | 727.11 | 476.9 |
| ድሬዳዋ | 20.19 | 18.32 | 14.77 | 17.13 | 14.79 | 22.81 | 33.56 | 20.339 |
| ክልል ድምር | 695.5 | 886.51 | 1129.3 | 1357.6 | 1595.2 | 1555.1 | 1736.59 | 1279.4 |
| ፌዴራል | 3243.3 | 5026.2 | 5836.8 | 6525.0 | 7967.1 | 8315.3 | 8454.92 | 6481.2 |
| ክልልና ፌዴራል | 3938.8 | 5912.8 | 6966.1 | 7882.5 | 9562.3 | 9870.4 | 10191.5 | 7760.7 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

### 4.1.2 የውጭ አገር ገቢ / ብድር እና እርዳታ/

በአገር ውስጥ ያለው ገቢ በቂ በማይሆንበት ጊዜ እና ለተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ማካሄጃ ፣ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ፣ ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት ለመውጣት የውጭ ፋይናንስ ያስፈልጋል። ስለሆነም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገር ብድርና

እርዳታ አስፈላጊ ይሆናል። ብድሩ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ በሌለው ፍጆታ ላይ ከዋለ ግን የዕዳ ጫናን ያመጣል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 17/1989 በአንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 መሠረት የሚከተሉትን ደንግጓል።

1. የገንዘብ ሚኒስትሩ ተፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተገቢው ጊዜ የመበደርን አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ያደረገ እና ወጪን መቀነስን ከተረጋጋ ወጪ ጋር ባመዛዘነ አፈፃፀም መምራት የሚያስችል የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ እንዲመሠረት ማድረግ አለበት
2. ብድር በአጠቃላዩ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትሉ በተለይም በገንዘብ ፖሊሲ ወይም በክፍያ ሚዛን ላይ የሚፈጥር አለመረጋጋትን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን መከላከል በሚያስችል መንገድ መተዳደር ይኖርበታል።

የዉጭ አበዳሪዎች በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን እነሱም

1. የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች /Multilateral/
2. የተለያዩ መንግሥታት /Bilateral/
3. የንግድ ድርጅቶች/Commercial/ ናቸው።

ከ1983 በፊት ዋንኛ አበዳሪዎች የዓለም ባንክ አካል የሆነው ዓለም አቀፍ የልማት ማህበርና የአፍሪካ ልማት ባንክ ፤ የቀድሞ ሶቪየት ኅብረት፤ ጣሊያን፤ አሜሪካና፤ ጀርመን፤ ዋንኞቹ የነበሩ ሲሆኑ ከ1983 ወዲህ ግን አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ዋንኞቹ አበዳሪዎቻችን ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ድህነት ለሚቀንስ የዕድገት ፕሮግራም /Poverty Reduction Growth Facility/ የዉጭ ምንዛሪ ጉድለት ማሟያ በ3 ዓመት ጊዜ ዉስጥ የሚያልቅ ዶላር አበድሯል። አዳዲስ ብድሮች ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የተወሰዱ ቢሆንም ከተለያዩ የንግድ አበዳሪዎች እና አገሮች የዕዳ ቅነሳ በመገኘቱ በደርግ ዘመን መጨረሻና በሽግግር መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ የነበረዉ 8.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በአሁኑ ጊዜ ወደ 5.5 ቢሊዮን ዝቅ ብሏል።

የዉጭ ብድር የሂሣብ አወቃቀር በዉጭ ብድር ወጪያቸዉ የሚሸፈኑ የወጪ ዓይነቶች የራሳቸዉ የብድር መለያ ቁጥር እንዲኖራቸዉ የሚያደርግ ሲሆን በበጀት መጠየቂያ

አበዳሪዉ ተለይቶ እንዲታወቅ፤ የፕሮጀክቱ ስም እንዲጠቀስ እና ለእያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት በሥራ ክፍል እና/ወይም በፕሮጀክት ደረጃ የሚሰጠዉ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን እንዲመለከት መደረግ አለበት፡፡ የዉጭ ብድር የሂሣብ አወቃቀር የሚከተሉት መለያ ቁጥሮች አሉት፡፡

ሠንጠረዥ 3

የዉጭ ብድር የሂሣብ አወቃቀር

| መለያ ቁጥሮች | የዉጭ ብድር ምድቦች |
|---|---|
| 3100 እስከ 3199 | የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ፕሮጀክቶች |
| 3200 እስከ 3599 | የኢኮኖሚ ፕሮጀክቶች |
| 3600 እስከ 3799 | የማህበራዊ ፕሮጀክቶች |
| 3800 እስከ 3849 | ሌሎች ፕሮጀክቶች |
| 3850 እስከ 3899 | የካዉንተር ፓርት ብድር |
| 3900 እስከ 3999 | ሊሎች |

መንግስት የበጀት ጉድለትን ለማሟላት ከአገር ዉስጥ ባንኮች እና ድርጅቶችም ብድር ይወስዳል፡፡ ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደዉ ቀጥታ ብድርና በየጊዜዉ በሚሸጠዉ የግምጃ ቤት ሰነድ /Treasury Bill/ የሚገኘዉ ብድር የአጭር ጊዜ ብድር በመሆኑ በየጊዜዉ የሚከፈል ነዉ፡፡ ነገር ግን የመንግስት ቦንድ በመሸጥ የሚገኘዉ ብድር ግን በመካከለኛና በረዥም ጊዜ የሚከፈል ነዉ፡፡

ዓለም ባንክና አይ.ኤም.ኤፍ ተበዳሪ አገሮች የሚያገኙት የዕዳ ቅነሳ ከድህነት መቀነስ ፕሮግራማቸዉ ጋር እንዲያያዝ ፕሮግራም የነደፉ ሲሆን ለዕዳ ክፍያ ይዉል የነበረዉ ገንዘብ ለድህነት መቀነሻ ፕሮግራሞች እንዲዉል የሚያደርግ ነዉ፡፡ በመሆኑም መንግስት የሚበደራቸዉ ብድሮች የኢኮኖሚ ጠቀሜታቸዉ ከፍተኛ የሆኑ እና የዉጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅማቸዉ ታይቶ ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ብቻ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም መንግስት ከፍተኛ ጫናን የማያስከትሉ ኮንሴሽናል ብድሮችን /ዝቅተኛ የወለድ ተመን ያላቸዉን/ እና የችሮታ ጊዜ ጨምሮ በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ ብድሮችን ብቻ መበደር ይኖርበታል፡፡ ሂፒክ ኢኒሼቲቭ /HIPCs initiative/ በመባል የሚታወቀዉ የዕዳ ማቃለያ ፕሮግራም ከፍተኛ የዕዳ ጫና ላለባቸዉ ድሃ አገሮች ዘላቂ የሆነ የዕዳ ጫናን ለማስወገድ ተብሎ የተነደፈ ፕሮግራም ሲሆን የፓሪስ ክለብ

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

አበዳሪ አገሮች ሲሰጡዋቸዉ ከነበሩት ነባር /Traditional/ የዕዳ ማቃለያ ዘዴዎች በስፋትና በጥልቀት የሚበልጥ ሲሆን የዕዳ ቅነሳዉም የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችን ብድር ጨምሮ የሁሉንም አበዳሪዎች ያጠቃልላል።

የዉጭእርዳታ በ2000 የሂሣብ አወቃቀር መደቦች ስር የሚታይ ሲሆን ቀጥሎ በተመለከተዉ ሠንጠረዥ ቀርቧል። የመለያ ቁጥሮች በጀትን ለማደራጀት የሚያገለግሉትን አራቱን የዘርፍ የበጀት አደረጃጀቶችን አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ እና ሌሎችን መሠረት በማድረግ እያንዳንዱ ፕሮጀክት የተለየ ቁጥር እንዲኖረዉ ያደርገዋል።

ሠንጠረዥ 5

የዉጭ እርዳታ የሂሣብ አወቃቀር

| መለያ ቁጥር | የዉጭ እርዳታ ምድቦች |
|---|---|
| 2100 - 2199 | የአስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ፕሮጀክቶች |
| 2200 - 2599 | የኢኮኖሚ ፕሮጀክቶች |
| 2600 - 2799 | የማህበራዊ ፕሮጀክቶች |
| 2800 - 2849 | ሌሎች ፕሮጀክቶች |
| 2850 - 2899 | የካዉንተር ፓርት ፈንድ |
| 2900 - 2949 | የዉጭ ንግድ ማረጋጊያ እርዳታ |
| 2950 - 2999 | ሌሎች |

በእርዳታ/ በብድር የራሳቸዉ የሆነ መለያ ቁጥር መስጠት በዉጪ እርዳታ ለሚደገፍ ፕሮጀክቶች ምዝገባ እና ክትትል ይረዳል። የተለየ የመንግስት የእርዳታ/ የብድር መለያ ቁጥር በመስጠት በበጀት ዉስጥ ለሥራ ክፍል እና ለፕሮጀክት የበጀት ምድቦች የወጪ ዓይነቶች የተሸፈኑበትን የዉጭ የፋይናንስ ምንጭ ለይቶ ማመልከት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 6

የመንግስት የገቢ ዕድገት/በአማካይ/

| | 1977-1983 | 1984 | 1985-1992 |
|---|---|---|---|
| የታክስ ገቢ | 3.2 | -21.2 | 19.7 |
| ቀጥታ ታክስ | 6.4 | -20.2 | 18.1 |
| የገቢ ግብር | -10.4 | 0.5 | 10.5 |
| የኪራይ ገቢ ግብር | | | 135.6 |
| የትርፍ ግብር | 15.7 | -18.4 | 19.7 |
| የመሬት ግብር | 6.6 | -92.0 | 163.4 |
| ከካፒታል ገቢ | | | 301.1 |
| ከከተማ ቦታ የሊዝ | | | 27.4 |
| ሌሎች | 27.6 | -53.3 | 39.6 |
| | | -29.5 | |
| ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች | 5.6 | -31.6 | 13.7 |
| ሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክስ | 4.8 | -10.4 | 11.5 |
| ከአገልግሎት ሽያጭ ታክስ | | -2.2 | 34.5 |
| ቴምብር ቀረጥ | -31.1 | -9.5 | 18.5 |
| | | | |
| የዉጭ ንግድ ታክስ | 0.4 | -9.5 | 28.7 |
| ከገቢ ዕቃዎች ታክስ | 7.3 | -7.3 | 28.1 |
| ከወጭ ዕቃዎች ታክስ | -15.8 | -55.5 | 71.9 |
| | | | |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 5.0 | -9.7 | 29.2 |
| ከመንግስት ንብረት | 4.7 | -14.6 | 31.3 |
| ሌሎች | 9.6 | -4.0 | 36.0 |
| | | | |
| የአገር ዉስጥ ገቢ | 3.2 | -18.4 | 21.0 |
| እርዳታ | 4.5 | 17.2 | 20.9 |
| የአገር ዉስጥ ገቢና እርዳታ | 2.2 | -13.2 | 20.0 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

## 4.2 የወጪ በጀት

የወጪ በጀት የተጀመረው መንግሥት ከሕዝብ በግብር መልክ የወሰደውን /የሰበሰበውን/ ገንዘብ በትክክለኛው እና ለሕዝብ እድገት አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ማዋሉን ለማረጋገጥ መሆኑን የታሪክ ማህደራት ይመሰክራሉ። እ.ኤ.አ በ1688 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር የመብት ሕግ/Bill of Rights/ ከወጣ በኋላ፤ የተቋቋመው ሕዝባዊ ሸንጎ ኀላፊነት የወጪውን በጀት ተመንና ድልድል በማድረግ በዝርዝር የመወሰን፤ በተፈቀደውም መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን መቆጣጠር መጀመሩ ለወጪ በጀት ክስተት ምክንያትነቱ ይገለፃል። በአሜሪካ ሀገር /No taxation without representation/ የሚለው መርህ በጀትን በመወሰን ረገድ ሥልጣኑ የሕዝብ ምክር ቤት ወይም የሕግ አውጭው አካል መሆኑን የሚለየው ሕግ በሕገ መንግሥት ላይ እንዲታይ መደረጉ ይህ ሥርዓት የሕዝብን መብት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እየያዘ መምጣቱን ያመለክታል።

ኢትዮጵያ ካፒታል እና መደበኛ በጀት በሚል የሚለይ ጥምር የበጀት ሥርዓት አላት። የአንድ የመንግሥት መ/ቤት የካፒታል በጀት በዋናኝነት የሚደራጀው በፕሮግራሞች እና በፕሮጀክቶች ሲሆን፤ የመደበኛ በጀቱ ደግሞ በዋናኝነት የሚደራጀው በሥራ ክፍሎች ደረጃ ነው።

### 4.2.1 መደበኛ በጀት

በመደበኛ በጀት የሚጠቃለሉት ደመወዝና ስራ ማስኬጃ ሲሆኑ የአገር ዉስጥና የዉጭ ብድር ወጪንም ይጨምራል። የመደበኛ በጀት ጥያቄ ሶስት የፋይናንስ ምንጮች አሉት እነሱም

1. የመንግስት ግምጃ ቤት
2. የደርጅት ገቢ እና
3. እርዳታ ናቸዉ።

እስከአሁን ድረስ መደበኛ በጀት በገንዘብ ሚኒስቴር በሚገኘዉ የበጀት መምሪያ የሚዘጋጅ ሲሆን የበጀት ዝግጅት ሂደትም የሚከተሉትን ደረጃዎች የተከተለ ነዉ። /Budget process 1998/

- የበጀት ጥሪ

ገንዘብ ሚኒስቴር ድምር የመደበኛ በጀቱን አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ያቀርባል:: በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ከታየ በኋላ የበጀት ጣሪያዉ ለመንግስት መ/ቤቶች ይላካል::

የበጀት ጣሪያዉም የሚያካትታቸዉ የሚከተሉትን ነዉ::

1. የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ፤
2. የመደበኛ በጀቱን ጣሪያ ፤
3. በበጀቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን፤
4. የበጀት ጥያቄ የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን፤ እና
5. የመደበኛ በጀት ጥያቄ አዘገጃጀት እና የማቀረቢያ ቅፆች ዝርዝር መመሪያ ናቸዉ::

- የበጀት ጥያቄ ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ

የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጥያቄአቸዉን የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለባቸዉ ሲሆን አጠቃላዩን የፋይናንስ ምንጭ መሠረት በማድረግ የሥራ እቅዳቸዉን እና ፕ ሮግራማቸዉን ከበጀት ጣሪያዉ ጋር እንዲመጣጠን ማድረግ እና ለፕሮጀክቶቻቸዉ እና ለሥራ ክፍሎቻቸዉ የሥራ እቅድ ማስፈፀሚያ ያስፈልጋል የተባለዉን የዋጋ ስሌት የሚያስረዳ መግለጫ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: በመሆኑም የበጀት ስሚ ከመካሄዱ በፊት የባለበጀት መስሪያ ቤቶች መደበኛ የበጀት ጥያቄአቸዉን ለገንዘብ ሚኒስቴር አቅርበዉ ይወያያሉ:: ይህም ዉይይት የሚካሄደዉ በገንዘብ ሚኒስቴር ዉስጥ ካለዉ የበጀት መምሪያ ነዉ:: በዚህ ዉይይት ወቅት መ/ቤቶች ከጣሪያ በላይ አቅርበዉ ከሆነ ያቀረቡበትን በቂ ምክንያት ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ የአገሪቱን አቅም ግምት ዉስጥ በማስገባት የሚጠየቀዉ በጀት ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ ለሚገባ፤ ፈጽሞ ሊቀሩ አይችሉም በሚባሉ እና በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ይዉላሉ ለተባሉ ፕሮግራሞች እና ሥራዎች መሆን አለበት::

- የበጀት ስሚ

በበጀት ስሚ ግዜ ሚኒስትሮች እና ምክትል ሚኒስትሮች፤ የመስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች፤ የበጀት ባለሙያዎች ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከባለበጀት መ/ቤቶች የሚገኙ ሲሆን ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ጣሪያዉ እንዲቀየርላቸዉ አሳማኝ ምክንያት ካላቸዉ ሊከራከሩ ይችላሉ:: ዉይይቱም የሚያተኩረዉ በፖሊሲዎች፤ በፕሮግራሞች እና በዋጋ ላይ ሲሆን አስፈላጊ ከሆነ በእያንዳንዱ የበጀት ዓይነትም ሊሆን ይችላል::

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

- የበጀት ድጋፍ በገንዘብ ሚኒስቴር

ከበጀት ስሚ በኋላ በገንዘብ ሚኒስቴር ዉስጥ ያለዉ የበጀት ኮሚቴ የበጀት ድጋፍ ያካሂዳል፡፡ በበጀት ድጋፍ ወቅት ለእያንዳንዱ የወጪ መደብ የቀረበዉ የበጀት ጥያቄ የጥሪ መመሪያ ዉስጥ በተዘረዘረዉ መሠረት የሚግቡ አመጣጥና ስሌት ትክክል መሆኑን ማየት፣ ከበጀት ጥሪዉ ጋር ተያይዘዉ የተላኩ ፎርሞችንና ቅፆች በትክክል ተሞልተዉ መቅረባቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የባለበጀት መ/ቤቶች በጀት ከበጀቱ ባረያ ከበለበ ለስምምነት ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ይላካል፡፡ በተጨማሪም በተጠየቀዉ በጀት በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ልዩ ልዩ መምሪያዎች ወይም የሥራ ክፍሎች /ንዑስ አርእስቶች/ በሙሉ መካተታቸዉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በፌደራሉ መንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን የመደበኛ በጀት ጥያቄዎች፣ በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚተላለፍለትን የካፒታል በጀት እና ከብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ድጎማ ጥያቄዎች መርምሮ የፌደራሉን መንግስት የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ገንዘብ ሚኒስቴር ከአስተያየቱ ጋር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

- በጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት

በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የተደገፈዉ በጀት በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ለኢኮኖሚ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ምክትል ሚኒስትር፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት እና ለአስተዳድሮች ከቀረበ በኋላ እና ከባለ በጀት መ/ቤቶች ጋር ከተወያዩበት በኋላ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመግለጫ ጋር ይቀርባል፡፡ በጀቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከታየ በኋላ ለዉይይት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይቀርባል፡፡

- በጀት በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት በጀቱ ከፀደቀ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ጠቅላላ ጉባዔዉ ዉይይት ካደረገ በኋላ ለአስተያየት ወደ በጀት ኮሚቴዉ ይመራል፡፡ የምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች አባላት በሚገኙበት በበጀት ኮሚቴዉ ሰብሳቢነት መግለጫዎች ይሰጣሉ ለሚቀርቡት ጥያቄዎችም በገንዘብ ሚኒስቴርና በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ባለሙያዎች መልሶች በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡ በመጨረሻም በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ያለዉ የበጀት ኮሚቴ አጥንቶ ከአስተያየት ጋር ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

- በጀት ማፅደቅ እና በነጋሪት ጋዜጣ ማዉጣት

በጀቱ በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ከፀደቀ በኋላ በፕሬዜዳንቱ ተፈርሞ አዋጅ ሆኖ በነጋሪት ጋዜጣ ይወጣል:: የገንዘብ ሚኒስቴር ለባለበጀት መ/ቤቶች የሚቀጥለዉን ዓመት በጀታቸዉን በ መግለጫ 3/1 እንዲያዉቁት የሚያደርግ ሲሆን ይህዉ መግለጫ በገንዘብ ሚኒስቴር ለሚገኘዉ የትሬዥሪ መምሪያ ለክፍያ እንዲረዳ ይላካል:: ነገር ግን ባለበጀት መ/ቤቶች መግለጫዉ እስከሚደርሳቸዉ ድረስ ያለፈዉን ዓመት 1/12ኛ በጀታቸዉን መጠቀም ይችላሉ::

ዓመታዊ በጀት አራት ዋና ዋና ነገሮችን የሚይዝ ሲሆን እነሱም

1. የፋይናንስ ምንጮችን ግምት/ የአገር ዉስጥ ገቢ፣ የዉጭ እርዳታና የዉጪ ብድር
2. ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚሰጠዉን ድጎማ
3. መደበኛ በጀት/ ይህም መደበኛ ወጪን እና ወጪዉ የሚሸፈንበትን የፋይናንስ ምንጭ ያጠቃልላል
4. ካፒታል በጀት/ ይህም የካፒታል ወጪን እና ወጪዉ የሚሸፈንበትን የፋይናንስ ምንጭ ይጨምራል::

የወጪዉ አመዳደብም በሚከተሉት ዘርፍ /አገልግሎት/ ተለይቶ የሚታይ ነዉ::

1. የመደበኛ በጀት
    - 1.1 ጠቅላላ አገልግሎት
    - 1.2 የኢኮኖሚ አገልግሎት
    - 1.3 የሶሻል አገልግሎት
    - 1.4 ሌሎች
2. የካፒታል በጀት
    - 2.1 የኢኮኖሚ ልማት
    - 2.2 የሶሻል ልማት
    - 2.3 ሌሎች

በየዓመቱ እየተዘጋጀ የሚወጣዉ የበጀት ነጋሪት ጋዜጣ ከላይ የተመለከቱትን ጠቅላላ ፕሮግራሞች ቅደም ተከተል ይዞ የሚወጣ ሲሆን፣ ዝርዝሮቹ በአርዕስት /ፕሮግራም/፣ንዑስ አርእስት/ንዑስ ፕሮግራም እና በዋና የሂሣብ መደቦች ይመለከታሉ:: የበጀት ኮድ ሲሰጥ ለምሳሌ የሕግና ፍትህ ሚኒስቴር በመደበኛ በጀት አመዳደብ ዉስጥ ራሱን የቻለ ፕሮግራም/አርእስት/ ስለሆነ የኮድ ቁ. 121 ተሰጥቶታል:: የሂሣብ ዋና መደብ በአንድ ንዑስ

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

አርእስት ሥር ሆኖ በዉስጡ የሂሣብ መደቦች ያሉት ነዉ፡፡ የሂሣብ ዋና መደብ የሂሣብ መደቦችን ማጠቃለያ ነዉ ለማለት ይቻላል፡፡

- በጀት ድልድል

የባለበጀት መ/ቤቶች በጀታቸዉን ካወቁ በኋላ የበጀት ድልድላቸዉን እና የሥራ እቅዳቸዉን በገንዘብ ሚኒስቴር ለሚገኘዉ የበጀት መምሪያ ያቀርባሉ፡፡ የበጀት መምሪያም የበጀት ድልድሉን ካጠና በኋላ ለትሬዠሪ መምሪያ ክፍያ እንዲፈፀም ያስተላልፋል፡፡

1. የመደበኛ ወጪ በጀት ድልድል ማስታወቂያ በቅጽ ገ/በማ/3/1
2. የካፒታል ወጪ በጀት ድልድል ማስታወቂያ በቅጽ ገ/በማ/3/2
3. የሥራ መደብ ዝርዝር መደልደያ በቅጽ ገ/በማ/21

ቅጽ ገ/በማ/3/1 በገንዘብ ሚኒስቴር በጀት መምሪያ አማካኝነት የሚሞላ የመደበኛ ወጪ በጀት ድልድል ማስታወቂያ ሲሆን፣ መስሪያ ቤቶችም በሚሰጣቸዉ የበጀት ድልድል መመሪያ መሠረት የመደበኛ ወጪ በጀታቸዉን አዉቀዉ አንዳንድ ማስተካከያዎችን ካደረጉ በኋላ ክፍያ እንዲፈፀም ለክፋይ ክፍሉ በበጀት መምሪያ ፀድቆ የሚተላለፍበት ቅፁ ነዉ፡፡ ቅፁ ገ/በማ/3/2 በኢኮኖሚና ልማት ትብብር ሚኒስቴር የሚሞላ የልማት/የካፒታል/ በጀት ድልድል ማስታወቂያ ሲሆን፣ የልማት መስሪያ ቤቶችም የልማት በጀት ድልድላቸዉን የሚያዉቁበት እና ለክፋይ ክፍሉ በበጀት መምሪያ ፀድቆ የሚተላለፍበት ነዉ፡፡

ሠንጠረዥ 7

የክልሎች እና የፌደራል መንግሥት የመደበኛ ወጪ /በሚሊዮን ብር/

| ዓ.ም/ክልል | 1986 | 1987 | 1988 | 1989 | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 118.56 | 160.69 | 167.1 | 182.46 | 205.5 | 209.44 | 205.14 |
| አፋር | 45.34 | 52.49 | 48.89 | 30.47 | 58.55 | 101.12 | 80.37 |
| አማራ | 369.99 | 479.96 | 505.52 | 540.71 | 586.94 | 648.42 | 573.97 |
| ኦሮሚያ | 572.85 | 662.95 | 836.5 | 818.75 | 914.54 | 947.34 | 924.37 |
| ሶማሌ | 38.43 | 67.6 | 53.98 | 70.14 | 65.03 | 79.92 | 101.63 |
| ቤ.ጉሻንጉል | 28.22 | 39.98 | 42.64 | 43.14 | 57.18 | 70.54 | 78.54 |
| ደ.ብ.ብ.ሕ | 288.08 | 376.85 | 436.15 | 446.19 | 458.34 | 553.97 | 484.29 |
| ጋምቤላ | 23.69 | 33.08 | 48.44 | 43.01 | 53.18 | 63.94 | 59.9 |
| ሐረር | 16.52 | 26.4 | 29.18 | 29.81 | 38.23 | 41.11 | 41.8 |
| አ.አ | 166.13 | 223.34 | 277.99 | 269.7 | 342.78 | 442.2 | 404.39 |
| ድሬዳዋ | 20.87 | 22.38 | 24.15 | 23.9 | 28.43 | 35.63 | 30.52 |
| ክልል ድምር | 1688.7 | 2145.7 | 2470.5 | 2498.3 | 2808.7 | 3193.6 | 2984.9 |
| ፌደራል | 2710.9 | 3069.8 | 3109.7 | 3238.9 | 7514.4 | 9521.9 | 9540.7 |
| ክልልና ፌደራል | 4399.6 | 5215.6 | 5580.2 | 5737.2 | 10323 | 12716 | 12525.6 |

ምንጭ፡ ገንዘብ ሚኒስቴር

- የበጀት ዝውውር

የበጀት ዝውውር በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፡፡


1. ባለፉት ዓመታት የፀደቀ ፕሮጀክትን ያልተጠናቀቁ ዕዳዎች ለመክፈል በጀት የሚያስፈልግ በማይሆንበት ጊዜ ይህ በጀት በሚከተለው አይነት ይመደባል፡፡
    - ለዚህ ዓላማ የሚያስፈልገው በጀት ከመንግስት መስሪያ ቤቱ የካፒታል በጀት በሚደረግ ዝውውር የሚሸፈን ከሆነ ዝውውሩ በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር መፈቀድ አለበት፡፡
    - ለዚህ ዓላማ የሚያስፈልገው በጀት ከአጠቃላዩ የካፒታል በጀት ጣሪያ ውስጥ የአንድን የመንግሥት መስሪያ ቤት የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት በማዛዋወር የሚሸፈን ከሆነ፣ ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በሚቀርብ ሃሳብ መሠረት ዝውውሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መፈቀድ አለበት፡፡

2. ከአንድ የመንግሥት መስሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት የመደበኛ በጀት ዝዉዉር ሊፈፀም የሚችለዉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቅድ ነዉ።

- የተስተካከለ በጀት

የተስተካከለ በጀት ማለት በመጀመሪያ በኮንግሬት ጋዜጣ በጥቅልም ሆነ በዝርዝር ከተፈቀደዉ በጀት የተደረገዉን ለዉጥ የያዘዉ በጀት ነዉ። በተፈቀደዉም በጀት ላይ ያሉ ለዉጦች ከተደመሩ ወይንም ከተቀነሱ በኋላ የሚታየዉ መጠን የተስተካከለ በጀትን ይሰጣል።

## የፌዴራል መንግስት የመደበኛ በጀት ዝግጅት በገንዘብ ሚኒስቴር



### 4.2.2 የካፒታል በጀት

የካፒታል በጀት በኢኮኖሚ ልማት እና ትብብር ሚኒስቴር የሚዘጋጅ ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁ . 46/1989 መሠረት የኢኮኖሚያ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ወቅታዊ በሆነወር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የመጀመሪያ ዓመት ላይ ያልታተተ ማናቸዉም ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት በካፒታል በጀት ዉስጥ አይካተቱም:: ማናቸዉም ፕሮጀክት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቅ አለበት:: የመንግስት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀ በኃላ በተከታዩ ዓመት ሥራ ላይ ሊዉል የሚገባ አዲስ ፕሮጀክት ያጋጠመ እንደሆነ ይህ አዲስ ፕሮጀክት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቅ አለበት::

የካፒታል በጀት አራት የፋይናንስ ምንጮች ሲኖሩት እነሱም

1. የመንግስት ግምጃ ቤት
2. የደርጅት ገቢ
3. እርዳታ እና
4. ብድር ናቸዉ::

ሠንጠረዥ 8

የካፒታል ወጪ

| | 1977-1984 | 1985-1992 |
|---|---|---|
| ኢኮኖሚ | 90.75 | 73.32 |
| እርሻ | 25.76 | 10.79 |
| ተፈጥሮ ሃብት | 14.13 | 12.85 |
| ማዕድን | 19.74 | 12.28 |
| ኢንዱስትሪ | 13.41 | 8.28 |
| ንግድ | 0.66 | 0.09 |
| መንገድ ሥራ | 7.23 | 20.01 |
| መጓጓዣ | 7.74 | 7.33 |
| ሌሎች | 2.46 | 1.67 |
| ሶሻል | 6.93 | 20.63 |
| ትምህርት | 3.04 | 10.19 |
| ጤና | 2.34 | 4.56 |
| የከተማ ልማት | 1.22 | 3.96 |
| የሕዝብ ደህንነት | 0.33 | 1.92 |
| ሌሎች | 2.32 | 6.05 |
| ድምር | 100.00 | 100.00 |

ምንጭ  የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር

የካፒታል በጀት ቅድመ ዝግጅት ስራዎች አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚና የፊሲካል ማእቀፍ እንዲዘጋጅ ማድረግ ሲሆን በዚህም አሰራር መጀመሪያ ሊኖር የሚችለዉ ጠቅላላ ሀብት /ከመደበኛ ገቢ፤ ከካዉንተር ፓርት ፈንድና ከዉጭ ፋይናንስ ይገመታል፡፡ ከዚህም ዉስጥ የፌዴራል መንግሥት ወጪንና ለክልሎች ሊሰጥ የሚችለዉ የበጀት ድጎማ ይለያል፡፡ በፌዴራል መንግስት ወጪ ዉስጥ የመደበኛ፤ የካፒታል ወጪም በጣሪያነት ሊኖር የሚችለዉ የበጀት ግምት ይዘጋጃል፡፡ በዚህም መሠረት በአስፈፃሚዉ መስሪያ ቤቶች በሚቀርበዉ የበጀት ጥያቄና ከመንግሥት ግምጃ ቤት በሚቀመጠዉ ጣሪያ መካከል ልዩነት ይኖራል፡፡ ስለዚህ የበጀት ጥያቄዎች ግምገማ ወቅት አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎችን በመጠቀም ልዩነቶች እንዲጠቡ ይደረጋል፡፡

የቀረበዉን የበጀት ጥያቄ ከአቅም ጋር ለማጣጣም እንዲሁም የሚቀርቡ አዳዲስ ኘ ሮጀክቶች ተገቢዉ የኘሮጀክት ጥናት የተደረገባቸዉና ተደግፈዉ የቀረቡ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ግምገማ የሚካሄድ ሲሆን ግምገማዉ በቅድሚያ የሚያተኩረዉ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ ኘሮጀክቶችን በመለየት እና በበጀት ዓመቱ ሊኖር ከሚችለዉ የመንግሥት ግምጃ ቤት ፋይናንስ ጋር ተገናዝቦ ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት የበጀት ድጋፉ የሚከተለዉን ቅድም ተከተል መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ ነዉ፡፡

1. ነባር ኘሮጀክቶች ሆነዉ ኮንትራት የተገባላቸዉና በዉጭ ፋይናንስ የሚካሄዱ በተጓዳኝ ከመንግሥት ግምጃ ቤት በጀት የሚፈልጉ ኘሮጀክቶች
2. በመንግሥት ግምጃ ቤት ብቻ የሚካሄዱ ሆነዉ በዉጭ ኮንትራክተር የሚካሄዱ ኘ ሮጀክቶች
3. በመንግሥት ግምጃ ቤት ብቻ የሚካሄዱ ሆነዉ በሃገር ዉስጥ ኮንትራክተር የሚካሄዱ ኘሮጀክቶች
4. ኮንትራት የሌላቸዉ ሆነዉ ግን ሥራቸዉ ሊቋረጥ የማይችሉ ኘሮጀክቶች
5. በአጠቃላይ ደግሞ የነባር ኘሮጀክቶችን የአፈፃፀም ሁኔታ
6. ከመንግሥት ፖሊስና ስትራቴጅ አኳያ ቅድሚያ በተሰጣቸዉ የልማት ዘርፎች ተጠንተዉ የቀረቡ አዲስ ኘሮጀክቶችን በመለየት
7. በድርጅት ገቢ ሊካሄዱ የሚችሉትን ከበጀት በማዉጣት
8. ወደ ግንባታ የሚሸጋገሩ ኘሮጀክቶች ቅድመ ዝግጅት አጠናቅቀዉ ወደ ግንባታ የሚገቡበትን ጊዜ በማሰብ

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

በመንግሥት ፖሊሲ ቅድሚያ የተሰጣቸዉን እንድም ሙሉ በሙሉ ባለመደገፍ ወይንም በዝቅተኛ መጠን ፍላጎታቸዉን በበጀት በማካተት የሚቀረበዉን የበጀት ጥያቄ ወደ ጣሪያዉ በማቅረብ

ሠንጠረዥ 9

ለ1994 በጀት ዓመት የተደገፉ የካፒታል ፕሮጀክቶች አይነትና ብዛት በክፍለ ኢኮኖሚ

| ተራ ቁ | ክፍለ ኢኮኖሚ | የተደገፈ | | | ድርሻ በመቶ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ነባር | አዲስ | ድምር | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 277 | 54 | 331 | 100.0 |
| | **ኢኮኖሚ ልማት** | 195 | 32 | 227 | 68.6 |
| 1 | ግብርና ልማት | 57 | | 57 | 17.2 |
| 2 | ዉሃ ሃብት | 11 | 3 | 14 | 4.2 |
| 3 | ማዕድን | 7 | 4 | 11 | 3.3 |
| 4 | ኢነርጅ | 13 | 2 | 15 | 4.5 |
| 5 | ኢንዱስትሪ | 2 | 1 | 3 | 0.9 |
| 6 | መንገድ ኮንስትራክሽን | 83 | 16 | 99 | 29.9 |
| 7 | ሳይንስና ቴክኖሎጅ | 4 | | 4 | 1.2 |
| .8 | ትራንስፖርትና መገናኛ | 18 | 6 | 24 | 7.3 |
| | **ሶሻል ልማት** | 52 | 16 | 68 | 20.5 |
| 9 | ትምህርት | 17 | 14 | 31 | 9.4 |
| 10 | ጤና | 28 | | 28 | 8.5 |
| 11 | ከተማ ልማትና ቤት | 2 | | 2 | 0.6 |
| 12 | ማኅበራዊ ደኅንነት | 2 | | 2 | 0.6 |
| 13 | ባሕል | 3 | 2 | 5 | 1.5 |
| | **ጠቅላላ ልማት** | 30 | 6 | 36 | 10.9 |
| 14 | ካርታ | 2 | | 2 | 0.6 |
| 15 | እስታትስቲክስ | 2 | | 2 | 0.6 |
| 16 | የአስተዳደር ሕንፃዎች | 23 | 3 | 26 | 7.9 |
| 17 | ሌሎች | 3 | 3 | 6 | 1.8 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

የተደገፈ በጀት ክፍለ ኢኮኖሚ ስርጭት የ1994 የፌዴራል መንግስት የካፒታል በጀት ድልድል እንደ አለፉት ዓመታት ሁሉ የመሠረተ ልማት አዉታሮችን በማስፋፋት ላይ ያመዘነ ነዉ:: ስለሆነም ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸዉ እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የመንገድ፤ የትራንስፖርትና መገናኛ፤ የግብርና፤ እና የትምህርት ክፍለ ኢኮኖሚዎች ናቸዉ:: የትምህርት፤ የጤናና የግብርና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት ከሚካሄድት በተጨማሪ ከፍተኛ በጀት ያላቸዉ በርካታ ፕሮጀክቶች በክልሎች ይካሄዳሉ::

ሠንጠረዥ 10

ለ1994 በጀት ዓመት የተደገፉ የካፒታል ፕሮጀክቶች በዋና ዋና ክፍለ ኢኮኖሚ

| ሴክተር | ከመንግሥት ግ/ቤት | ፐርሰንት | ከሁሉም ምንጭ | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ግብርና ልማት | 83.3 | 6.9 | 346.6 | 11.2 |
| ዉሃ ሃብት | 48.0 | 4.0 | 194.6 | 6.3 |
| ማዕድንና ኢነርጅ | 30.0 | 2.5 | 35.0 | 1.1 |
| መንገድ ኮንስትራክሽን | 501.8 | 41.7 | 1445.0 | 46.6 |
| ትራንስፖርትና መገናኛ | 86.4 | 7.2 | 365.3 | 11.8 |
| ትምህርት | 199.8 | 16.6 | 329.7 | 10.6 |
| ጤና | 2.7 | 0.2 | 29.0 | 0.9 |
| እስታትስቲክስ | 135.4 | 11.2 | 135.4 | 4.4 |
| ሌሎች | 116.6 | 9.7 | 219.1 | 7.1 |
| ድምር | 1204.0 | 100.0 | 3099.7 | 100.0 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለዉ ከመንግሥት ግምጃ ቤት አጠቃላይ መጠን መንገድ ኮንስትራክሽን፤ ትራንስፖርትና መገናኛ፤ የግብርና፤ እና ትምህርት 72.4 በመቶ ድርሻ አላቸዉ:: በ1994 ከመንግስት ግ/ቤት ከተደገፈዉ ካፒታል በጀት መንገድ 41.7 ከመቶ ድርሻ ያለዉ ሲሆን ከአጠቃላይ የፌደራል መንግስት ካፒታል በጀት 46.6 ከመቶ ድርሻ አለዉ::

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚዘጋጀዉ የካፒታል በጀት ዝግጅት የሚከተሉትን ደረጃዎች የተከተለ ነዉ።

- የካፒታል በጀት ጥሪ

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለባለበጀት መስሪያ ቤቶች በየዓመቱ የካፒታል በጀት ጣሪያቸዉን በበጀት ጥሪ የሚያስተላልፍ ሲሆን ሀገራዊ የካፒታል በጀት ጣሪያዉ ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በቀረበ ማብራሪያ መሰረት በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ የሚወሰን ነዉ። ነገር ግን የሴክተር ጣሪያ ሀገራዊ ጣራያዉ ከተወሰነ በኋላ በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ይወሰናል። የበጀት ጥሪዉ ዋና ዓላማ የባለበጀት መስሪያ ቤቶች በተወሰነ ቀን በጀታቸዉን እንዲያቀርቡ ሲሆን የሚያቀርቡትም በወጪ መደብ እና በወጪ ምንጭ ለይተዉ ነዉ።

- የካፒታል በጀት ጥናት

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሴክተር መምሪያዎች ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች የቀረበላቸዉን የበጀት ጥያቄ አጥንተዉ ልዩነት ካለ ዉይይት ያካሄዳሉ። ከዚህ በኋላ ሴክተር መምሪያዎች የመጀመሪያ ዙር የተደገፈ በጀቱን በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለሚገኘዉ በጀት መምሪያ ያቀርባሉ። የበጀት መምሪያም ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮና ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ቢሮ ተዉጣጥቶ ለተቋቋመዉ የበጀት ኮሚቴ ያቀርባል።

- የካፒታል በጀት ስሚ

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመራ ስብሰባ የባለበጀት መስሪያ ቤቶች የካፒታል በጀታቸዉን ከትክክለኛ መረጃ ጋር የሚያቀርቡ ሲሆን የካፒታል በጀት ስሚዉ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ
መስሪያ ቤቱ ፕሮጀክቱን በተግባር የማስፈፀም አቅም
ፕሮጀክቱ ሀገሪቱ ለልማት ቅድሚያ ከሰጠቻቸዉ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑ
የዋጋ ሁኔታ እና
የክልል ክፍፍል ናቸዉ።

- ካፒታል በጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት እና በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት

የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጀት በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ከተጠና በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስተካከያ ካደረገ በኋላ የካፒታል በጀት የመጀመሪያዉ ደረጃ ይፀድቃል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት የካፒታል በጀትን የመጀመሪያ ድራፍት ለሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።

- የካፒታል በጀትን ማሳወቅ እና በነጋሪት ጋዜጣ ማዉጣት

በጀት ከፀደቀ በኋላ ኢኮኖሚ ልማት እና ትብብር ሚኒስቴር የመጨረሻዉን የካፒታል በጀት ለሚመለከታቸዉ የባለበጀት መስሪያ ቤቶች ያሳዉቃል። በጀቱ ሕጋዊነት የሚያገኘ ዉ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተመ በኋላ ሲሆን ይህም የሚሆነዉ ከነሀሴ እስከ መስከረም ባለዉ ግዜ ዉስጥ ይሆናል።

ሠንጠረዥ 11

የክልሎች እና የፌዴራል መንግሥት የካፒታል ወጪ /በሚልዮን ብር/


1986 እስከ 1992

| ዓ.ም/ክልል | 1986 | 1987 | 1988 | 1989 | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 118.51 | 137.2 | 131.38 | 211.74 | 170.86 | 229.2 | 50.44 |
| አፋር | 35.56 | 21 | 65.49 | 36.16 | 102.2 | 192.34 | 81.88 |
| አማራ | 136.64 | 210.01 | 222.1 | 300.36 | 210.96 | 441.66 | 102.46 |
| ኦሮምያ | 164.93 | 243.91 | 281.95 | 426.28 | 328.85 | 546.42 | 139.47 |
| ሶማሌ | 33.8 | 43.18 | 109.72 | 111.73 | 175.26 | 341.38 | 134.84 |
| ቤንሻንጉል | 27.06 | 29.69 | 51.02 | 58.38 | 94.05 | 133.88 | 72.94 |
| ደ.ብ.ብ.ሕ | 87.44 | 183.77 | 230.65 | 234.57 | 138.77 | 382.64 | 67.91 |
| ጋምቤላ | 21.71 | 16.89 | 35.37 | 39.67 | 40.26 | 98.4 | 43.84 |
| ሐረር | 0.45 | 11.17 | 11.76 | 9.49 | 43.43 | 59.75 | 20.42 |
| አ.አ | 124.4 | 164.53 | 182.14 | 196.39 | 379.19 | 753.66 | 236.24 |
| ድሬዳዋ | 0.58 | 4.16 | 4.9 | 9.66 | 18.46 | 30.51 | 8.86 |
| ክልል ድምር | 751.08 | 1065.5 | 1326.5 | 1634.4 | 1702.3 | 3209.8 | 959.3 |
| ፌዴራል | 1943.3 | 2091 | 2236.2 | 2452.5 | 1782 | 2709.1 | 1889.6 |
| ክልልና ፌዴራል | 2694.4 | 3156.5 | 3562.6 | 4086.9 | 3484.3 | 5918.9 | 2848.9 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴር

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

የፌዴራል መንግስት የካፒታል በጀት ዝግጅት በኢኮኖሚ ልማት እና ትብብር



## 5. የበጀት ምድብ

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱ አካል የሆነዉ የወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ንዑስ ፕሮግራም የማሻሻያ ዋንኛዉ አላማ የፋይናንስ ቁጥጥርን ማሻሻል ነዉ፡፡

1. አሁን እየተሠራበት ያለዉ የበጀት ሥርዓት ድክመቶች
2. በህግ የተደገፈ የበጀት የጊዜ ሠሌዳ አለመኖር
3. ግልጽና የተሟላ የበጀት ወይም የሂሳብ አወቃቀር አለመኖር
4. በአሠራር ላይ ከበጀት ዉጭ የሆነ ወጪዎች መታየት
5. ተመጣጣኝ የወጪ ቅንጅት አለመኖር /ለምሳሌ/ ከፍተኛ ደመወዝ መድቦ በጣም ወጊስን የሆነ የስራ ማስኬጃ ማስቀመጥ
6. ለበጀት ዝግጅት የሚረዱ ዘዴዎች አለመኖር ፣ ለበጀት አፈፃፀምና ክትትልና ግምገማ የሚረዳ ስልቶች በብቃት አለመኖር፣

ጠንካራ የሆነ የፋይናንስ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖር ናቸዉ፡፡

እነዚህን ድክመቶች ለማስወገድ ለካፒታል እና ለመደበኛ ወጪዎች ወጥ የሆነ የበጀት ቅፆችን ማዘጋጀት ፣ ጣምራ የበጀት ጥሪ ማከናወን፣ ወጥ የሆኑ የወጪ መደቦች መጠቀም፣ የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት እና የወጪ ማእከሎችን በመመሥረት በጀት በወጪ ማእከሉች እንዲገናኝ ማድረግ ከተወሰዱ እርምጃዎች ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

አንድ ወጥ አደረጃጀት ሲባል ለካፒታልም ሆነ ለመደበኛ በጀት በገንዘብ ሚኒስቴርና በኢኮኖሚያ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በኩል የሚያዘዉ መለያ ቁጥር አንድ አይነት ሀሬstandard/ መሆን ማለት ነዉ፡፡ አንድ ወጥ የሆነ መረጃ የገቢ መለያ ቁጥር መስጠት፣ አንድ አይነት ፎርማት መከተል ማለት ነዉ፡፡

1. የአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ፕሮጀክቶችና የስራ ክፍሎች የመደበኛና የካፒታል ወጪ በማይለዋወጥ ሁኔታ እንዲቀርብ የበጀት ምድብ ወጥ የሆነ መለያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡ ይህም በጀትን
2. ለመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በፕሮግራሞቻቸዉ ፣ በስራ ክፍሎቻቸዉ፣ በንዑስ ፕሮግራሞቻቸዉ እና በፕሮጀክቶቻቸዉ አኳያ ለይቶ ለማሳየት
3. የወጪ ማእከሎችን ለመመስረት እና

ለስራ ክፍል እና ለፕሮጀክት የበጀት ምድቦች የተፈቀደዉን ገንዘብ ምንጭ በዝርዝር የወጪ ዓይነት ለይቶ ለማሳየት ይረዳል፡፡

የበጀት ምድቦች 11 ወነ መለያ ቁጥሮች ሲኖሮአቸዉ እነዚህም የሥልጣን ወሰን፤ የበጀት ዓይነት፤ ዘርፍ፤ ንዑስ ዘርፍ፤ የመንግስት መስሪያ ቤት፤ ኘሮግራም፤ የሥራ ክፍል፤ንዑስ ኘሮግራም፤ ኘሮጀክት፤ የወጪ ዓይነት እና የፋይናንስ ምንጭ ናቸው።

ሠንጠረዥ 12

የበጀት አደረጃጀት የመደበኛ በጀት ምሳሌ

| የሂሣብ መደብ | የበጀት ምድብ | የአኀዞች ብዛት | ምሳሌ | መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| | የሥልጣን ወሰን | 2 | ፌዴራል | 15 |
| | የበጀት ዓይነት | 1 | መደበኛ | 1 |
| አርእስት | ዘርፍ | 1 | የኢኮኖሚ ዘርፍ | 200 |
| | ንዑስ ዘርፍ | 1 | የግብርና ልማት | 10 |
| | የመንግስት መ/ቤት | 1 | የግብርና ሚኒስቴር | 1 |
| ንዑስ አርእስት | ኘሮግራም | 1 | | 0 |
| ንዑስ ንዑስ አርእስት | የሥራ ክፍል | 2 | አስተዳደርናጠቅላላ አገልግሉት | 01 |
| ንዑስ ንዑስ ንዑስ አርእስት | ንዑስ ኘሮግራም | 2 | | 00 |
| ንዑስ ንዑስ ንዑስ ንዑስ አርእስት | ኘሮጀክት | 3 | | 000 |
| ዓይነት | የወጪ መደብ | 4 | የቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ | 6111 |
| ምንጭ | የፋይናንስ ምንጭ | 4 | | 0000 |

የተሟላ የወጪ መለያ ቁጥር 15/1/211/0/01/00/000/6111/0000

ሠንጠረዥ 13

የበጀት አደረጃጀት የካፒታል በጀት ምሳሌ

| የሂሣብ መደብ | የበጀት ምድብ | የአኀዞች ብዛት | ምሳሌ | መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| | የሥልጣን ወሰን | 2 | ፌዴራል | 15 |
| | የበጀት ዓይነት | 1 | ካፒታል | 1 |
| አርእስት | ዘርፍ | 1 | የማህበራዊ ዘርፍ | 300 |
| | ንዑስ ዘርፍ | 1 | ትምህርት | 10 |
| | የመንግስት መ/ቤት | 1 | ትምህርት ሚኒስቴር | 1 |
| ንዑስ አርእስት | ፕሮግራም | 1 | ከፍተኛ ትምህርት | 2 |
| ንዑስ ንዑስ አርእስት | የሥራ ክፍል | 2 | ወንዶ ገነት የደን ኮሌጅ | 20 |
| ንዑስ ንዑስ ንዑስ አርእስት | ንዑስ ፕሮግራም | 2 | የትምህርት አገልግሎት | 01 |
| ንዑስ ንዑስ ንዑስ ንዑስ አርእስት | ፕሮጀክት | 3 | የወንዶ ገነት ኮሌጅ ኮ. ማጠ. | 114 |
| ዓይነት | የወጪ መደብ | 4 | የመኖሪያ ሕንፃ ግንባታ | 6322 |
| ምንጭ | የፋይናንስ ምንጭ | 4 | የስዊድን ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት እርዳታ | 2641 |

የተማላ የወጪ መለያ ቁጥር 15/2/311/2/20/01/114/6322/2641

በበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂዉ መሠረት የበጀት ምድቦችን በአንድ ወጥነት ለመጠቀም 8 የበጀት አመዳደብ መርሆዎች ተገልፀዋል፡፡ እነሱም

1. ምድቦች እና መለያ ቁጥሮች ልዩነቶችን በበቂ ሁኔታ ማሳየት
2. ምድቦች እና መለያ ቁጥሮች ግልጽ ፤ ትርጉም የሚሰጡና የማይለዋወጡ
3. ምድቦች እና መለያ ቁጥሮች ከዓመት ወደ ዓመት የማይለዋወጡ
4. ምድቦች እና መለያ ቁጥሮች ከበጀት ዓይነት ገለልተኛ መሆን የበጀት ምድቦች የአንድን የመንግስት መስሪያ ቤት በጀት በዋና ዋና መዋቅሮች እና ፕሮግራሞች ለይተዉ ማሳየት
5. የካፒታል እና የመደበኛ ወጪዎች በወጪ ማእከል እንዲገናኙ
6. ምድብ እና መለያ ቁጥሮች የመንግስት ኢንቨስትመንት ፕሮግራምን፣ በጀትን እና ሂሳብን እንዲያገናኙ እና

7. የበጀት ምድቦች እና በቋሚነት የሚሠራባቸዉ መለያ ቁጥሮች በማእከላዊነት በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚዘጋጁ መሆን እንደሚኖርባቸዉ ይገለፃል፡፡

## 6. የዕቅድና የበጀት ጊዜ

በኢትዮጵያ የበጀት ሥርዓት ዉስጥ የሚታየዉ ዋንኛዉ ድክመት የበጀት ተግባሮችን የሚገልጽ እና የሚከናወኑበትም የጊዜ ሠንጠረዥ የሚያሳይ አስገዳጅ የሆነ የጊዜ ሠሌዳ ያለመኖሩ ነዉ፡፡ የበጀት ዝግጅት በእቅድ ዑደት ዉጤት ላይ የሚደገፍ ስለሆነ ዉጤታማ የሆነ የበጀት ዝግጅት እንዲኖር ለማድረግ አስገዳጅ የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ በሥራ ላይ እንዲዉል በበጀት ማሻሻያ ጥናቱ ተወስኖአል፡፡ /ሠንጠረዥ 12/.

እቅድ የአንድ አገር የኢኮኖሚና የሰሻል ወጪዎች የሚታይበት ዝርዝር ሲሆን በጀት ደግሞ እነዚህ ወጪዎች በፕሮግራም ተከፋፍለዉ በየበጀት ዘመኑ በተግባር መተርጎማቸዉን ማረጋገጫ መሣሪያ ነዉ፡፡ ስለሆነም በጀት የእቅድ ማስፈፀሚያ መሣሪያ ነዉ፡፡ እቅድ የአንድን መስሪያ ቤት አላማ የሚያሳዉቅ እና አላማዉን ከግብ ለማድረስ ደረጃ በደረጃ መከናወን ያለባቸዉን ተግባሮች የሚዘረዝር ሲሆን እያንዳንዱ መስሪያ ቤት ለሚቀጥለዉ በጀት ዓመት በጀት በሚያዘጋጅበት ጊዜ በቅድሚያ የሥራ እቅድ ማዘጋጀት የበጀት ጥያቄዉም በሥራ እቅድ መመስረት አለበት፡፡

መስሪያ ቤቱ የሥራ እቅድ/ፕሮግራም ተመርኩዞ በጀት የሚጠይቅ ከሆነ የበጀት ጥናት ድጋፍና፣ ማፀደቅ ሥራ ቀላል ይሆናል፡፡ በተቃራኒዉ የበጀቱ ጥያቄ በሥራ እቅድ ያልተደገፈ ከሆነ ግን የበጀት ጥናቱ ዉስብስብና አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በጀት ለተጠየቀለት አመት ለማከናወን የታቀደ የሥራ ፕሮግራም በሥራ ላይ ካለዉ ካለፋት አመታት የሥራ እቅድ አፈፃፀም ጋር ተመዛዝኖ በዝርዝር መረጃ ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

የበጀት ዑደት ዓመታዊ በጀት ማዘጋጀትን፣መመርመርን፣ ማጽደቅን፣ መፍቀድን እና በሥራ ላይ ማዋልን የሚያካትት ነዉ፡፡ በጀት የመንግሥትን ወጪ ሁሉ ባካተተ ሁኔታ ማስተዳደር አለበት የሚለዉ የተሟላ በጀት ቁልፍ መርህ ነዉ፡፡

በኢትዮጵያ የሚታወቀዉ የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ነዉ፡፡ ከ1951 ዓ.ም በፊት ግን የበጀት ሰሌዳና አዲስ አመት አንድ ላይ ይሆን እንደነበር ማለትም በመስከረም ወር ይጀመር እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ የፊናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 67/1989 በአንቀጽ 16 ለየዓመቱ የተፈቀደዉ በጀት እስከ ሰኔ 30 ቀን በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ፀድቶ፤ ሁሉም ባለበጀት መስሪያ ቤቶች እስከ ሀምሌ 7 ቀን እንዲያዉቁት ይደረጋል የሚል ሲሆን የፊናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 በአንቀፁ 15 ላይ የገንዘብ ሚኒስቴር ከኢኮኖሚና ልማት ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የበጀት የጊዜ ሰሌዳን የሚወስን መመሪያ ያወጣል ይላል፡፡

በጀት በመሠረቱ የተከታታይነት ጠባይ ያለዉ የሥራ ዘርፍ ነዉ፡፡ ከአንድኛዉ ዓመት ወደሚቀጥለዉ ዓመት ሽግግር ሲያደርግ በተወሰነዉ የበጀት ወቅት ዉስጥ እየደጋገመ የሚሄድባቸዉ ሂደቶች አሉ፡፡ የበጀት ማሻሻያ ጥናት የፋይናንስ እቅድን ከበጀት አፈቃቀድ ጋር የሚያገናኝ አዲስ የፋይናንስ እቅድ የጊዜ ሠሌዳ እንዲኖር ያደረገ ሲሆን በጀቱን፤ ከዝግጅት እስከ መፍቀድ እና የአፈፃፀም መርሃ ግብር እስከ ማዘጋጀት ድረስ የሚያልፍባቸዉን የተለያዩ ደረጃዎች እና የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ሠሌዳ ወስኖአል፡፡ /የሚቀጥለዉን ሠንጠረዥ ይመልከቱ/

ሠንጠረዥ 14

የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ

| | የጊዜ ሠሌዳ | |
|---|---|---|
| የዕቅድ ዑደት/ ክፍል/ደረጃ | በኢትዮጵያ | በአዉሮፓ |
| 1. ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ዕቅድ | ከሐምሌ 1 ነሐሴ 15 | ጁላይ 8 ኦገስት 21 |
| 2. ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ፕሮግራም | ከመስከረም 14 ታህሳስ 29 | ሴፕቴምበር 25 ጃንዋሪ 8 |
| 3. ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ | ከጳጉሜ 1 ታህሳስ 29 | ሴፕቴምበር 6 ጃንዋሪ 8 |
| የበጀት ዑደት/ክፍል/ደረጃ | | |
| ሀ. በአስፈፃሚ አካላት የሚደረግ ዝግጅት | | |
| 1. የበጀት ዝግጅት | ከመስከረም 20 መጋቢት 6 | ኦክቶበር 1 ማርች 15 |
| 2. ለክልል ድጎማ ቀመር ማዘጋጀት | ከመስከረም 20 ህዳር 5 | ኦክቶበር 1 ኖቬምበር 15 |
| 3. የድጎማዉን ግምት ማስታወቅ | ከታህሳስ 30 ጥር 7 | ጃንዋሪ 9 ጃንዋሪ 16 |
| 4. የበጀት ጥሪ | ከታህሳስ 30 ጥር 29 | ጃንዋሪ 9 ፌብሩዋሪ 17 |
| 5. የበጀት ጥያቄ | ከጥር 30 መጋቢት 22 | ፌብሩዋሪ 8 ማርች 31 |
| 6. የተደገፈዉ በጀት ዝግጅት | ከመጋቢት 23 ግንቦት 29 | ኤፕሪል 1 ጁን 6 |
| 7. የተደገፈዉ በጀት ማፅደቅ | ከግንቦት 30 ሰኔ 13 | ጁን 7 ጁን 20 |
| ለ. በሕግ አዉጪዉ መፅደቅ | | |
| 8. የክልሎችን ድጎማ ቀመር ማፅደቅ | ከህዳር 6 ታህሳስ 5 | ኖቬምበር 16 ዲሴምበር 15 |
| 9. የተደገፈዉ በጀት ክፍል 4 ማፅደቅ | ከሰኔ 14 ሰኔ 30 | ጁን 21 ጁላይ 7 |
| 10. የፀደቀዉ በጀት በሥራ ላይ እንዲዉል መፍቀድ | ከሰኔ 14 ሰኔ 30 | ጁን 21 ጁላይ 7 |
| ሐ. በአስፈፃሚዉ አካል ሥራ ላይ ማዋል | | |
| 11. የታወጀዉን በጀት ማስታወቅ | ከሐምሌ 1 ሐምሌ 8 | ጁላይ 8 ጁላይ 15 |
| 12. የታወጀዉን በጀት መደልደል | ከሐምሌ 1 ነሐሴ 9 | ጁላይ 8 ኦገስት 15 |
| 13. የታወጀዉን በጀት ሥራ ላይ ማዋል | ከሐምሌ 9 ሐምሌ 30 /የሚቀጥለዉ በጀት ዓመት/ | ጁላይ 16 ኦገስት 6 /የሚቀጥለዉ በጀተ ዓመት |
| መ. በአስፈፃሚዉ አካል ሂሳቡን መመርመር/ ክትትል ማድረግ | | |

ምንጭ የበጀት ማሻሻያ ጥናት 1992

ሠንጠረዥ 15

የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ እና ኀላፊነት የተሰጣቸዉ መስሪያ ቤቶች

| ዑደት/ክፍል/ደረጃ | ኀላፊነት የተሰጠዉ መስሪያ ቤት/መስሪያ ቤቶች |
|---|---|
| የዕቅድ ዑደት/ክፍል/ደረጃ | |
| 1. ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ዕቅድ | ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 2. ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ፕሮግራም | ኢልትሚ እና የመንግሥት መስሪያ ቤቶች |
| 3. ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ | ገንዘብ ሚኒስቴር |
| የበጀት ዑደት/ክፍል/ደረጃ | |
| ሀ. በአስፈፃሚ አካላት የሚደረግ ዝግጅት | |
| 1. የበጀት ዝግጅት | የመንግሥት መስሪያ ቤቶች |
| 2. ለክልል ድጎማ ቀመር ማዘጋጀት | ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 3. የድጎማዉን ግምት ማስታወቅ | ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 4. የበጀት ጥሪ | ገንዘብ ሚኒስቴር/ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 5. የበጀት ጥያቄ | የመንግሥት መስሪያ ቤቶች |
| 6. የተደገፈዉ በጀት ዝግጅት | ገንዘብ ሚኒስቴር/ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 7. የተደገፈዉ በጀት ማፅደቅ | ጠ/ሚ/ጽ/ቤት/ሚኒስትሮች ምክር ቤት |
| ለ. በሕግ አዉጪዉ መፅደቅ | |
| 8. የክልሎችን ድጎማ ቀመር ማፅደቅ | የፌዴሬሽን ምክር ቤት |
| 9. የተደገፈዉ በጀት ክፍል 4 ማፅደቅ | የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት |
| 10. የፀደቀዉ በጀት በሥራ ላይ እንዲዉል መፍቀድ | የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት |
| ሐ. በአስፈፃሚዉ አካል ሥራ ላይ ማዋል | |
| 11. የታወጀዉን በጀት ማስታወቅ | ገንዘብ ሚኒስቴር/ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር |
| 12. የታወጀዉን በጀት መደልደል | ገንዘብ ሚኒስቴር/ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር/የመንግሥት መስሪያ ቤቶች |
| 13. የታወጀዉን በጀት ሥራ ላይ ማዋል | የመንግሥት መስሪያ ቤቶች |
| መ. በአስፈፃሚዉ አካል ሂሳቡን መመርመር/ ክትትል ማድረግ | |

ምንጭ የበጀት ማሻሻያ ጥናት 1992

የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተዉ የእቅድና የበጀት ዑደት ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸዉ:: /የበጀት ማሻሻያ ጥናት 1992/

- ከአመት በላይ የሆነ ዕቅድ

በአሁኑ ወቅት በሚሠራበት የፋይናንስ አስተዳደር ላይ የሚታየዉ ድክመት የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶችን የፋይናንስ ፕሮግራም ዝግጅት የሚመራ ከአንድ አመት በላይ የሆነ ማዕቀፍ ያለማኖሩ ነዉ:: በመሆኑም በበጀት ማሻሻያ ጥናቱ መሠረት የብዙ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ማዕቀፍ የማዘጋጀት ኀላፊነት ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የተሰጠ ሲሆን በሚከተሉት ላይ የሦስት ዓመት ትንበያን ያቀርባል::

1. የኢኮኖሚ ዕድገት እና ጠቅላላ የሀገር ዉስጥ ምርት
2. የመንግስትን ወጪ እና ወጪዉ የሚሸፈንበትን የፋይናንስ ምንጭ
3. ለፌዴራል መንግስት ወጪዎች የተመደበዉን እና ለክልሉች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚደረገዉን አጠቃላይ ድጎማ ድልድል
4. የፌዴራል መንግስት የካፒታል እና የመደበኛ ወጪ ድልድል
5. የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የካፒታል ወጪ ድልድል

- ከአመት በላይ የሆነ ፕሮግራም

ከአንድ አመት በላይ የሆነ ፕሮግራም ዝግጅት የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የሚዘጋጅበት ሲሆን፤ ይህም የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገሪቱ ያላትን ሀብት መጠን፤ የሚፈቀድላቸዉ ገንዘብ የተሰጣቸዉ ተግባር የሚጠይቀዉን ወጪ ለመሸፈን መቻሉን እና ሥራቸዉን በተግባር ለማዋል አቅም ያላቸዉ መሆኑን ከግምት ዉስጥ በሚያስገባ ሁኔታ የመስሪያ ቤቱን ዓላማ ሊያስፈጽም በሚችል መንገድ ወጪን በቅደም ተከተል እንዲደለድሉ የሚጠይቅ ነዉ:: የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የሚያዘጋጁት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሲሆኑ፤ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የዝግጅቱና የማጠቃለሉን ሥራ ያስተባብራል::

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተገምግሞ ፤ ተሻሽሎና፤ ፀድቆ በሚኒስትሩ ጽ/ቤት በኩል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ ይቀርባል:: የፀደቀዉ የመንግስት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ይሠራጭና ለሚቀጥሉት ዓመታት የካፒታል በጀት ዝግጅት መሠረት ይሆናል::

- የፊሲካል ኘላን

የፊሲካል ኘላን የፌዴራል መንግሥት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ጣሪያ እንዲሁም የክልሉች እና የመስተዳድር ምክር ቤቶች ጠቅላላ የድጎማ ጣሪያ ይወስናል፡፡ የፊሲካል ኘ ላን የዕቅድ ዑደት መጠናቀቂያ ሲሆን ለበጀት ዑደት ደረጃዎች መነሻ ነዉ፡፡

- የበጀት ዑደት

1ኛ የበጀት ዝግጅት

በጀት ማዘጋጀት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ኀላፊነት ሲሆን ሶስት ተግባሮች አሉት፡፡ እነሱም የነጠላ ዋጋን ማዘጋጀት፤ ኘሮግራምን መገምገም እና የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት ናቸዉ፡፡ እነዚህ ተግባራት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጥያቄ በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚያከናዉኑአቸዉ ይሆናሉ፡፡ በበጀት ዝግጅት ሂደት ዉስጥ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጣሪያአቸዉን እንዲያዉቁ የሚደረግ ሲሆን ይህንን ጣሪያ ጠብቀዉ የሥራ ዕቅዳቸዉን መቀነስ እና ለሥራ ዕቅዳቸዉ የሚዉለዉን ወጪ አስልቶ በሰነድ መያዝ አንዱ ተግባር ነዉ፡፡

2ኛ የክልሉችን ድጎማ ቀመር ማዘጋጀት

ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለክልሎች ለሚደለደለዉ ድጎማ መሠረት የሚሆነዉን ቀመር የያዘ የዉሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

3ኛ የድጎማ ግምት ማስታወቅ

ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የፊሲካል ኘላን እና የክልሉችን ድጎማ ቀመር መሠረት በማድረግ ማሳወቂያዉን የሚያዘጋጅ ሲሆን ከታህሣሥ እስከ ጥር 7 ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች ይልካል፡፡

4ኛ የበጀት ጥሪ

የበጀት ጥሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጣሪያአቸዉን የሚያዉቁበት እና የበጀት ጥያቄአቸዉን እንዴት እና መቼ ማቅረብ እንዳለባቸዉ የሚገልፅ ነዉ፡፡ በበጀት ማሻሻያ ጥናቱ መሠረት በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢኮኖሚና ልማት ትብብር ሚኒስቴር ጣምራ የበጀት ጥሪ የሚተላለፋ ሲሆን የገንዘብ ሚኒስቴር የበጀት ጥሪዉን የማስተላለፍ እና የማዘጋጀት ኀላፊነት አለበት፡፡ የበጀት ጥሪ 7 ክፍሉች ያሉት ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

1. የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ግምት የሚያቀርቡበትን የመጨረሻ ቀን የሚጠቅሰዉ ክፍል
2. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በጀታቸዉን በሚየዘጋጁበት ጊዜ ከግምት ዉስጥ ሊያስገቡት የሚገባዉን የኢኮኖሚ ሁኔታ እና የፋይናንስ ዉሱንነት የሚያሳይ አጭር መግለጫ
3. የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጀታቸዉን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ሊመሩበት የሚገባዉን የመንግሥት ፖሊሲ/ ምሳሌ ያሉትን አገልግሉቶች ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም እና ለመጠበቅ የሚያስችል መደበኛ ወጪ መኖሩን ማረጋገጥ
4. የዉጭ እርዳታ እና ብድር የሚመሩበትን የአፈፃፀም ሥርዓት
5. ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀቶች ዝግጅት ለእያንዳንዱ አግባብ ያለዉን መመሪያ
6. የእያንዳንዱን የመንግሥት መስሪያ ቤት የወጪ በጀት ጣሪያ እና የፋይናንስ ምንጭ እና
7. የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ጥያቂዎች አቀራረብ መመሪያ እና የማቅረቢያ ቅፅ ናቸዉ::

5ኛ የበጀት ጥያቄ

የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበጀት ጥሪ ሲደርሳቸዉ የበጀት ጥያቄአቸዉን ያዘጋጃሉ:: የበጀት ጥያቄዉ ከበጀት ጣሪያዉ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሁለት ተግባሮችን ማከናወን አለባቸዉ:: እነሱም

- አጠቃላዩን የፋይናንስ ምንጭ መሠረት በማድረግ የሥራ ዕቅዳቸዉን እና ፕ ሮግራማቸዉን ከበጀት ጣሪያዉ ጋር እንዲመጣጠን ማድረግ እና
- ለፕሮጀክቶቻቸዉ እና ለሥራ ክፍሉቻቸዉ የሥራ ዕቅድ ማስፈፀሚያ ያስፈልጋል የተባለዉን ወጪ የዋጋ ስሌት የሚያስረዳ መግለጫ ማዘጋጀት ናቸዉ::

6ኛ የተደገፈዉን በጀት ማዘጋጀት

1. ይህ ዑደት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያቀረቡት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ጥያቄ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚመረመርበት፣ የሚስተካከልበት እና ወጪዉ በበጀታ ዉስጥ የሚጠቃለልበት ነዉ:: የተደገፈዉ በጀት በገንዘብ ሚኒስቴር ተጠቃሎ እንዲመረመር እና

እንዲፀድቅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቀርብ ሲሆን አራት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል። እነሱም

2. የፋይናንስ ምንጭ
3. ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚሰጠዉን ድጎማ
4. የመደበኛ በጀት እና
5. የካፒታል በጀት ናቸዉ።

7ኛ የተደገፈዉን በጀት ማፅደቅ

የተደገፈዉ በጀት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚፀድቅ ሲሆን አራት ተግባራት ይከናወናሉ። እነሱም

1. ወጪዉን ለመሸፈን ይገኛል ተብሎ የታሰበዉ የፋይናንስ ግምት አስተማማኝ መሆኑን መመርመር ፤
2. ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚሰጠዉን ጠቅላላ የድጎማ መጠን እንዲሁም የፌዴራል ወጪዎች እና የድጎማ መጠን መመርመር፤
3. በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የቅድሚያ አወሳሰን ቅደም ተከተል ወይም ማናቸዉም በመንግሥት ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል የተባለ አዲስ ጉዳይ በተደገፈዉ በጀት ዉስጥ መካተቱን ማረጋገጥ እና
4. ለመደበኛ ወጪ የተመደበዉ በጀት የመንግሥትን ፖሊሲ የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ነዉ።

8ኛ ለክልሎች የሚሰጠዉን የድጎማ ቀመር ማፅደቅ

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለክልሎች የሚሰጠዉን ድጎማ ቀመር የያዘ የዉሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመሩን ይመረምራል፤ ያፀድቃል።

9ኛ የተደገፈዉን በጀት ማፅደቅ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተደገፈዉን በጀት ይመረምራል፤ ያሻሽላል እንዲሁም ያፀድቃል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተደገፈዉን በጀት ካፀደቀዉ የፀደቀ በጀት ይሆናል።

10ኛ የፀደቀዉን በጀት መፍቀድ

የተፈቀደዉ ዓመታዊዉ በጀት የታወጀ በጀት ሆኖ በነጋሪት ጋዜጣ ይወጣል። የፀደቀዉ በጀት የሚፈቀደዉ በበጀት ዓይነት / የፌዴራል መንግሥት ጠቅላላ የካፒታል እና

የመደበኛ በጀት/ ፤ በጠቅላላ ድኅማ እና የእያንዳንዱን ክልል እና መስተዳድር ምክር ቤት ድኅማ በማሳየት ብቻ ነዉ። ከተፈቀደዉ ዓመታዊ በጀት በላይ ተጨማሪ ገንዘብ በሚያስፈልግበት ጊዜ አስፈፃሚ አካላት የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበዉ ወጪዉን የሚሸፍን፤ ተጨማሪ በጀት ማፅደቅ እና መፍቀድ አለበት

## 11ኛ የታወጀዉን በጀት ማስታወቅ

የገንዘብ ሚኒስቴር፤ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ፤ እና የፋይናንስ ቢሮዎች በወጪ ዓይነት በመዘርዘር የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እንዲያዉቁት ያደርጋሉ።

## 12ኛ የታወጀዉን በጀት መደልደል

በዚህ የበጀት ሁደት ጊዜ የወጪ ማዕከሎችን የሥራ ዕቅድ በታወጀዉ በጀት ዉስጥ ከተመለከቱት ጣሪያዎች ጋር ማስተካከል እና የፋይናንስ እና የፊዚካል መርሐ ግብር ማዘጋጀት ነዉ። የፋይናንስ የድርጊት መርሐ ግብር በየወሩ ይወጣል ተብሎ የታቀደዉን የገንዘብ መጠን የሚያመለክት ሲሆን፤ የፊዚካል የድርጊት መርሃ ግብር ደግሞ በእያንዳንዱ የወጪ ማዕከል ደረጃ በየወሩ ፍፃሜ ያገኛሉ ተብለዉ የታቀዱ ሥራዎችን ያሳያል።

## 13ኛ የታወጀዉን በጀት በሥራ ላይ ማዋል

የበጀት አፈፃፀም ተግባር የክፍያ ጥያቄዎችን ማስተናገድ፤ የበጀት ዝዉዉሮችን እና ተጨማሪ ድልድልን መመዝገብ፤ የፋይናንስ እና የፊዚካል የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚቀርብ ወርሃዊ ሪፖርት ማዘጋጀት ሲሆን በመካሄድ ላይ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች እንደሚተርፍ የሚጠበቀዉን ገንዘብ ለይቶ ማወቅ እና የሚተርፈዉን ገንዘብ ለሌሎች ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸዉ ሥራዎች ማዘዋወር ሌላዉ ተግባር ነዉ።

እንዲፀድቅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቀርብ ሲሆን አራት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል:: እነሱም

2. የፋይናንስ ምንጭ
3. ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚሰጠዉን ድጎማ
4. የመደበኛ በጀት እና
5. የካፒታል በጀት ናቸዉ::

7ኛ የተደገፈዉን በጀት ማፅደቅ

የተደገፈዉ በጀት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚፀድቅ ሲሆን አራት ተግባራት ይከናወናሉ:: እነሱም

1. ወጪዉን ለመሸፈን ይገኛል ተብሎ የታሰበዉ የፋይናንስ ግምት አስተማማኝ መሆኑን መመርመር ፤
2. ለክልሎች እና ለመስተዳድር ምክር ቤቶች የሚሰጠዉን ጠቅላላ የድጎማ መጠን እንዲሁም የፌዴራል ወጪዎች እና የድጎማ መጠን መመርመር፤
3. በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የቅድሚያ አወሳሰን ቅደም ተከተል ወይም ማናቸዉም በመንግሥት ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል የተባለ አዲስ ጉዳይ በተደገፈዉ በጀት ዉስጥ መካተቱን ማረጋገጥ እና
4. ለመደበኛ ወጪ የተመደበዉ በጀት የመንግሥትን ፖሊሲ የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ነዉ::

8ኛ ለክልሎች የሚሰጠዉን የድጎማ ቀመር ማፅደቅ

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለክልሎች የሚሰጠዉን ድጎማ ቀመር የያዘ የዉሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመሩን ይመረምራል፤ ያፀድቃል::

9ኛ የተደገፈዉን በጀት ማፅደቅ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተደገፈዉን በጀት ይመረምራል፤ ያሻሽላል እንዲሁም ያፀድቃል:: የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተደገፈዉን በጀት ካፀደቀዉ የፀደቀ በጀት ይሆናል::

10ኛ የፀደቀዉን በጀት መፍቀድ

የተፈቀደዉ ዓመታዊዉ በጀት የታወጀ በጀት ሆኖ በነጋሪት ጋዜጣ ይወጣል:: የፀደቀዉ በጀት የሚፈቀደዉ በበጀት ዓይነት / የፌዴራል መንግሥት ጠቅላላ የካፒታል እና

የመደበኛ በጀት/ ፤ በጠቅላላ ድንማ እና የእያንዳንዱን ክልል እና መስተዳድር ምክር ቤት ድንማ በማሳየት ብቻ ነዉ። ከተፈቀደዉ ዓመታዊ በጀት በላይ ተጨማሪ ገንዘብ በሚያስፈልግበት ጊዜ አስፈፃሚ አካላት የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርበዉ ወጪዉን የሚሸፍን፤ ተጨማሪ በጀት ማፅደቅ እና መፍቀድ አለበት

11ኛ የታወጀዉን በጀት ማስታወቅ

የገንዘብ ሚኒስቴር፤ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ፤ እና የፋይናንስ ቢሮዎች በወጪ ዓይነት በመዘርዘር የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እንዲያዉቁት ያደርጋሉ።

12ኛ የታወጀዉን በጀት መደልደል

በዚህ የበጀት ዑደት ጊዜ የወጪ ማዕከሎችን የሥራ ዕቅድ በታወጀዉ በጀት ዉስጥ ከተመለከቱት ጣሪያዎች ጋር ማስተካከል እና የፋይናንስ እና የፊዚካል መርሐ ግብር ማዘጋጀት ነዉ። የፋይናንስ የድርጊት መርሐ ግብር በየወሩ ይወጣል ተብሎ የታቀደዉን የገንዘብ መጠን የሚያመለከት ሲሆን፤ የፊዚካል የድርጊት መርሃ ግብር ደግሞ በእያንዳንዱ የወጪ ማዕከል ደረጃ በየወሩ ፍፃሜ ያገኛሉ ተብለዉ የታቀዱ ሥራዎችን ያሳያል።

13ኛ የታወጀዉን በጀት በሥራ ላይ ማዋል

የበጀት አፈፃፀም ተግባር የክፍያ ጥያቄዎችን ማስተናገድ፤ የበጀት ዝዉዉሮችን እና ተጨማሪ ድልድልን መመዝገብ፤ የፋይናንስ እና የፊዚካል የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚቀርብ ወርሃዊ ሪፖርት ማዘጋጀት ሲሆን በመካሄድ ላይ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች እንደሚተርፍ የሚጠበቀዉን ገንዘብ ለይቶ ማወቅ እና የሚተርፈዉን ገንዘብ ለሌሎች ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸዉ ሥራዎች ማዘዋወር ሌላዉ ተግባር ነዉ።

## 7. የመንግስት ሂሳብ አቀራረብ እና ቁጥጥር

ለባለበጀት መስሪያ ቤቶች የመደበኛና የካፒታል በጀት ክፍያ የሚፈጸመዉ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚገኘዉ የክፍያና ሂሳብ መምሪያ መረጃዎችን በመመርመር ሲሆን የባለበጀት መስሪያ ቤቶችም ወጪ የሚጠይቁት በፀደቀዉ የበጀት ዓይነት ነዉ::

ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

- ወርሃዊ ሪፖርት በመደበኛ ገቢ፣ መደበኛ ወጪ፣ ካፒታል ወጪና በክፍያና ሂሳብ መምሪያና በመ/ቤቱ የተደረገዉን የገንዘብ ልዉዉጥ
- አመታዊ ሪፖርት "ዝገባ ሪፖርት " ይህም የሚያመለክተዉ በተፈቀደዉ በጀት ክፍያና ሂሳብ ለመስሪያ ቤቱ የከፈለዉና በየመስሪያ ቤቱ የወጣዉን ትክክለኛ ወጪ ይይዛል::

በገንዘብ ሚኒስቴር የሚገኘዉ የማዕከላዊ ሂሣብ መምሪያም አመታዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚረዳዉን የመንግሥት ገቢና ወጪን ዳታ ያጠናቅራል:: በተጨማሪም የፖሊሲና ጥናት መምሪያም ወርሃዊ የገቢና የወጪን እና የወጪ አሸፋፈን ሪፖርት የሚያዘጋጅ ሲሆን መረጃዉን የሚያገኘዉም ከክፍያና ሂሣብ መምሪያ ነዉ::

በዚህም መሠረት የገንዘብ ሚኒስቴር የፌዴራል መንግስትን አመታዊ የገቢና የወጪ አፈፃፀም የሚያዘጋጅ ሲሆን ይህንንም መረጃ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለዋናዉ ኦዲተር መስሪያ ቤት ለምርመራ ያቀርባል ይህን በተመለከተ የፋናንስ አስተዳደር ሕጉ የገንዘብ ሚኒስቴር የበጀት ዓመቱን የሂሣብ ሪፖርት በማዘጋጀት በተቻለ ፍጥነት ያቀርባል በሚል አስቀምጦታል:: የገንዘብ ሚኒስቴር በየሶስት ወሩ እና በየወሩ የሚያዘጋጀዉን የሂሣብ ሪፖርትም ለሚመለከተዉ ክፍል ያቀርባል::
በአጠቃላይ የሚቀርበዉም የፋናንስ ሪፖርት ይዘት የሚከተለዉን ይዘት ይይዛል::

1. የሂሣብ መግለጫዎች

- የበጀት ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች
- የፌዴራል/የክልሉ መንግሥትን የበጀት ዓመቱ ገቢዎችን እና ወጪዎችን
- የተጠቃለለዉ ፈንድ
- የፌዴራል/የክልሉ መንግስት እዳዎች፣ዋስትና የተገባባቸዉን እና የሚጠበቁ ግዴታዎች

- ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደዉ፤ ወጪ የተደረገዉን እና ወጪ ያልተደረገዉን የገንዘብ መጠን
- የዘቀጠ ፈንድ ካለ እና
- የፌደራል/የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመቱን የፊናንስ እንቅስቃሴዎች እና አቋም የሚያሳዩ ሌሎች ሂሣቦች እና መረጃዎች

2. ዋናዉ ኦዲተር/የክልሉ የኦዲት ቢሮ የፊናንስ መግለጫን መርምሮ የሰጠዉን አስተያየት
3. አግባብነቱ የታመነበት ሌላ ተመሣሣይ መረጃ ናቸዉ።

የበጀት ዕቅድ የሚባለዉ በነጋሪት ጋዜጣ የሚታወጀዉ በጀት ሲሆን ከታወጀ በኃላ በቀጣይነት በትክክል በተያዘለት ፕሮግራም መሠረት መከናወኑን በሕግ መንግስቱ አንቀፅ 101 በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የሚያረጋግጠዉና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሒሳብ ኦዲት ሪፖርት የሚያቀርበዉ የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ነዉ። አጠቃላይ የሆነ የባለበጀት መስሪያ ቤቶችን የሂሣብ ምርመራ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚገኘ ዉ የኢንስፔክሽን መምሪያ የሚያካሂድ ሲሆን የዋናዉ ኦዲተር መስሪያ ቤትም ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ሂሣብ ይቆጣጠራል። ይህም ሂሣብን ብቻ መቆጣጠር ሳይሆን ገንቢ የሆኑ የሂሣብ አያያዝ እና አቀራረብን መስሪያ ቤቶች እንዲከተሉ ትምህርት ይሰጣል። በመስሪያ ቤቶች የሚፈፀመዉ ክፍያ በካሽ/ በጥሬ ገንዘብ/ ሲሆን በተፈቀደ በጀት መጠን ልክ የሚፈፀመዉ ክፍያ ወጪዉ እንደተፈፀመ በተገቢዉ ሂሣብ መደብ ይመዘገባል። ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ተዘጋጅቶ ለበጀት መምሪያ የሚደርስ ሲሆን ይህም የሂሣብ ሪፖርት ለሚቀጥለዉ በጀት ዘመን የበጀት ጥናት መረጃ ሆኖ ያገለግላል።

ለሂሣብ ሪፖርትም ይረዳ ዘንድ መንግስት የፋይናንስ አካላት/ የመንግስት መስሪያቤቶችን ፤ የገቢ ዓይነቶች፤ የዉጭ እርዳታ፤ የዉጭ ብድር፤ የጥሬ ገንዘብ ዝዉዉር፤ የአገር ዉስጥ ብድር እንዲሁም የወጪ ዓይነቶችን ዝርዝሮችን መዝግቦ የሚያሳይበት መለያ ቁጥር ያለዉ ሲሆን መለያ ቁጥሮችም የሚከተሉት ናቸዉ።

| መለያ ቁጥር | የወጪ ዓይነት |
|---|---|
| 0 999 | የመንግስት መ/ቤት በዘርፍ/ንዑስ ዘርፍ አደረጃጀት |
| 1000 1999 | የአገር ዉስጥ ገቢ ዓይነት |
| 2000 2999 | የዉጭ አገር እርዳታ |
| 3000 3999 | የዉጭ አገር ብድር |
| 4000 4999 | የጥሬ ገንዘብ ዝዉዉር |
| 5000 5999 | የአገር ዉስጥ ብድር |
| 6000 6999 | የወጪ መደብ ዓይነት |

በ6000 ዉስጥ ያሉት የወጪ መደቦች በሂሣብ ምድብ የወጪ ዓይነቶች ሲሆኑ እነሱም አራት ቁጥር ባለዉ በተለየ እና ወጥነት ባለዉ መለያ ቁጥር ይገለፃሉ። አራት የወጪ ዘርፎች ሲኖሩ እነሱም ሰብዓዊ የሆኑ አገልግሎቶች 6100፣ እቃዎች እና አገልግሎቶች 6200፣ ቋሚ ንብረት እና ኮንስትራክሽን 6300፣ እና ሌሎች ክፍያዎች 6400 ናቸዉ።መለያ ቁጥሮች ለማናቸዉም የወጪ ዓይነት እንዲያገለግሉ የተያዙ ሲሆን፤ ይህ ተከታታይ ቁጥር ለካፒታል እና ለመደበኛ በጀቶች እንዲሁም ከአገር ዉስጥ ወይም ከዉጭ አገር የገንዘብ ምንጮች ለሚሸፈኑ የወጪ ዓይነቶች የሚያገለግል ነዉ። / አባሪ ሁለት/.

## 8. የበጀት አስተዳደር ሥርዐት ከሕግ አንፃር

አንድ መንግስት ከሕዝቡ ጋር ስላለዉ ግንኙነት መነሻ የሚሆነዉ የሥራ መመሪያዉ የሀገሪቱ ሕገ መንግስት፤ ሕጎች፤ ደንቦች፤ ድንጋጌዎች፤ ወይም መመሪያዎች ናቸዉ:: ስለሆነም በአሁኑ ግዜ ለበጀት አስተዳደር ሕጋዊ መሠረቱ ሕገ መንግስቱ፤ የፋይናንስ ሕጉ እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ናቸዉ::

### 8.1 ሕገ መንግስት

1. የመንግስትን ስልጣን በመገደብ ረገድና የሕዝብንም መብት በማረጋገጥ ረገድ መሠረታዊ የሕግ አንቀፆች ተብለዉ የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸዉ::
2. ያለሕግ ከሕዝብ ማሰብሰብ እንደማይቻል ከመሰብሰብም የሚያስቀር ነገር አለመኖሩ
3. ያለበጀት አዋጅ /ሕግ/ ከሕዝብ የተሰበሰበዉን ወይም በሕዝበ ስም የተሰጠን ወጪ ማድረግ መንግስት እንደማይቻል .

በ1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የፌዴራል እና የክልል መንግስታትን ስልጣን እና ተግባር ግልጽ ያደረገ ሲሆን ክልሎች የራሳቸዉን በጀት እንደሚያስተዳድሩ ተገልፆል:: ሕገ መንግስቱ የሚከተለዉን ስልጣን እና ተግባር ግልጽ አድርጓል::

የፌዴራል መንግስት ስልጣንና ተግባር

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ቁ.4 መሠረት የፌዴራል መንግስት የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ፤ ስትራቴጂና እቅድ ያወጣል፤ ያስፈፀማል:: በአንቀፀ 51 ቁ .10 መሠረት ለፌዴራሉ መንግስት በተሰጡ የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ ይጥላል፤ ያስተዳድራል፤የፌዴራል መንግስት በጀት ያረቃል፤ ያፀድቃል፤ ያስተዳድራል:: ብሄራዊ ባንክን ያስተዳድራል፤ ገንዘብ ያትማል፤ ይበደራል፤ የዉጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልዉዉጥን ይቆጣጠራል:: ክልሎች ከዉስጥ ምንጮች ስለሚበደሩት ሁኔታ ሕግና መመሪያ ያወጣል::

- የክልል መንግስት

በአንቀጽ 52 ቁ . 2 መሠረት ለክልል በተሰጡ የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ ይጥላል፤ ያስተዳድራል። የክልሉን መንግስት በጀት ያረቃል፤ ያስተዳድራል።

- የሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት

በአንቀጽ 55 ለፌዴራል መንግስት በተከለለዉ የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፤ የፌዴራል መንግስት በጀት ያፀድቃል። የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፤ የማኅበራዊ፤ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፤ የፋናንስና የገንዘብ ፖሊሲን ያፀድቃል፤ ገንዘብን የብሄራዊ ባንክ አስተዳደርን፤ የዉጭ ምንዛሪንና ልዉዉጥን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ያወጣል።

- የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የክልሎችና የፌዴራሉ መንግስት የጋራ ተብለዉ የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግስት ለክልሉ ድጉማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል።

- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል። ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል። የገንዘብና የፋናንስ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤ ብሄራዊ ባንክን ያስተዳድራል፤ ገንዘብ ያትማል፤ ከሀገር ዉስጥና ከዉጭ ሀገር ይበደራል፤ የዉጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልዉዉጥን ይቆጣጠራል። የኢኮኖሚያዊ፤ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ ያስፈጽማል።

### 8.2 የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ

የፋናንስ ደንብ ሲባል አንድ መንግስት በስልጣን ክልሉ ዉስጥ በሕግ ለሚሰበስበዉ ገቢ እና ለሚያወጣዉ ወጪ እንዴት በተግባር እንደሚያወጣዉ ለራሱ የሚያወጣዉ የሥራ መመሪያ ነዉ። ለአንድ መንግስት የፋናንስ አስተዳደር ዋና መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለዉ በጀት ነዉ። ስለሆነም በጀት ከአንድ መንግስት የረጅም ጊዜ የልማት እቅድ ዉስጥ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም ነዉ።

## የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

የፌዴራል መንግስት በጀት አስተዳደር የሚመራዉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁ. 57/1989 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁ. 17/1989 እንዲሁም በገንዘብ ሚኒስትሩ በወጡ የፋይናንስ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ነዉ::

- ሕገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁ . 57/1989 ከተደነገገዉ ዉስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል::
- ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከአንድ የተጠቃለለ ፈንድ ብቻ ይከፈላሉ
- በዓይነት የሚሰጥ እርዳታ በዋጋ ተተምኖ በተጠቃለለዉ ፈንድ ይመዘገባል
- በሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ካልተፈቀደ በቀር ከተጠቃለለዉ ፈንድ መክፈል አይቻልም::
- በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ የታክስ ሥርዓቶች የተጣጣሙና ተመሳሳይ የታክስ መሠረት ያላቸዉ እንዲሆኑ

የገንዘብ ሚኒስቴሩ አገር አቀፍ የፊናንስ ፓሊሲ እና በሌሎች ሕጎችና ስምምነቶች የተደረገዉን የብድር ገደብ ግምት ዉስጥ በማስገባት የክልል መስተዳድሮች ሊበደሩ የሚችሉትን የገንዘብ መጠን መወሰን እንዲችል የክልል መስተዳድሮች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ መስጠት አለባቸዉ::

## 9. የአልተማከለ የፋይናንስ አስተዳድር በኢትዮጵያ

ክልሎችን ለማቋቋም አዋጅ የወጣዉ በ1984 በጀት ዓመት ቢሆንም ክልሎች ግን መዋቅር የጀመሩት የ1985 በጀት ዓመት ተደልድሎ ካበቃ በኃላ በመሆኑ የክልል መስተዳድሮች በአዲስ መልክ በጀት ማዘጋጀት የጀመሩት ከ1986 በጀት ዓመት ጀምሮ ነዉ:: አዋጅ ቁጥር 7/84 ክልሎች በየክልላቸዉ ታክስና ቀረጥ እንዲጥሉ የራሣቸዉን የገቢ ምንጭ እንዲያስተዳድሩና በጀታቸዉን እንዲፈቅዱ ደንግጓል::

### 9.1 የገቢ ክፍፍል

የገቢ ክፍፍል ከተለያዩ ምንጮች የሚገኘዉን እና መንግሥታዊ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችለዉን ገቢ በማእከል፣ በጋራና በክልል መካከል ለማደላደል፣ ክፍፍሉንም ለመወሰን ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 33/85 ወጥቶ ተግባራዊ ሲሆን፣ ከዚያም ወዲህ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ዉስጥ ተደንግጓ ይገኛል:: በማእከላዊ መንግስት እና በብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች መካከል የሚካሄደዉ የገቢ ክፍፍል የሚከተሉትን ዐበይት ዓላማዎች የያዘ ነዉ:: እነዚህም

- የማእከላዊ መንግስት እና ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች በሕግ የተሰጣቸዉን ኃላፊነቶችና ተግባሮች በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል
- ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች በራሳቸዉ አነሳሽነት አካባቢአቸዉን ለማልማት እና ለማሣደግ እንዲችሉ ማድረግ
- በክልሎች መካከል የሚታየዉን የልማት እና የኢኮኖሚ እድገት ልዩነት ማቀራረብ

ለክልሎች የጋራ ጠቀሜታ የሚሰጡ ተግባሮችን ለማበረታታት የሚሉ ናቸዉ:: እነዚህንም ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለገቢ ክፍፍሉ የሚከተሉት ዓቢይ ባሕሪያት መሠረት ሆነዉ ተወስደዋል::

- የገቢ ምንጭ ባለቤትነት
- የገቢ ምንጮች አገራዊና ክልላዊ ባሕሪ
- የታክስና የቀረጥ አሰባሰብና አተማመን አመቺነት
- የየክልሉን የሕዝብ ብዛት፣ የሀብት ሥርጭት እና የልማት ደረጃ እና
- ሌሎች ለተዋሀደና ለተመጣጠነ ኢኮኖሚ መሠረት የሆኑ መመዘኛዎች ናቸዉ::

የበጀት ዝግጅትና የፋይናንስ አስተዳደር

የገቢ አመዳደብ የተነሣበትን ዓላማ መሠረት በመንተራስ በአገሪቱ ዉስጥ ያሉትን ታክስና ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች፣ የማእከላዊ መንግሥት፣ የክልሎችና የጋራ በማለት ለይቶ ያስቀምጣል:: ይኸዉም የገቢ ክፍፍሉ የሚከተለዉ ነዉ::

1. የማእከላዊ መንግስት ገቢዎች

- በወጪና ገቢ እቃዎች ላይ የተጣለ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች
- ከማእከላዊ መንግስትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር
- በአገራዊ የሎተሪና ሌሎች የእድል ሙከራ ገቢዎች ላይ የሚሰበሰብ ታክስ
- በማእከላዊ መንግስት ባለቤትነት ሥር ከሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚሰበሰብ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ
- በአየር በባቡርና በባሕር ትራንስፖርት ገቢዎች ላይ የሚከፈል ታክስ
- በማእከላዊ መንግስት ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር
- በማእከላዊ የሽግግር መንግስት አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች
- የሞኖፖል ታክስ
- የቴምብር ሽያጭና ቀረጥ

2. የብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች ገቢዎች

- ከክልል መስተዳድሮችና ከድርጅቶች ተቀጣሪዎች እንዲሁም የማእከል ገቢ ወይም የጋራ ገቢ ተብለዉ ከተጠቀሱት ዉጭ ከሆኑት ሌሎች ተቀጣሪዎች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር
- የገጠር መሬት መጠቀሚያ ኪራይ
- ለግል የሚያርሱና በኅብረት ሥራ ማኅበራት ከተደራጁ ገበሬዎች የሚሰበሰብ የግብርና ሥራ ገቢ ግብር
- ከክልሉ ግለሰብ ነጋዴዎች የሚሰበሰብ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ
- በክልሉ ዉስጥ ዉሃ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር

- በክልል መስተዳድርና በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶች እና ሌሎች ንብረቶች ከሚገኝ ኪራይ ገቢ የሚሰበሰብ ግብር
- በከፍተኛ የማዕድን፤የፔትሮሊየም እና የጋዝ ሥራዎች የሚገኝ የገቢ ግብር የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን ሳይጨምር ከማዕድን ሥራዎች የሚሰበሰብ የማዕድን ገቢ ግብር፤ የሮያሊቲና የመሬት ክራይ ክፍያዎች
- በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች
- ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያዎች ናቸዉ።

## 3. የጋራ ገቢዎች

በማእከላዊ መንግስትና በክልል መስተዳድሮች መሀከል የሚከፋፈሉ ገቢዎች የጋራ ገቢዎች ተብለዉ ተለይተዋል። እነርሱም

- ማእከላዊ መንግስትና ክልሉች በጋራ ከሚያቋቁሞቸዉ የልማት ድርጅቶች የሚሰበሰብ የንግድ ትርፍ ግብር፤ የሥራ ግብር፤ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ
- ከድርጅቶች የሚሰበሰብ የንግድ ትርፍ ግብር፤ በባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የሚከፈል ግብር፤ የሽያጭ እና የኤክሣይዝ ታክስ
- ከከፍተኛ የማዕድን፤ ከማናቸዉም የፔትሮሊየም እና የጋዝ ሥራዎች የሚገኝ የገቢ ግብር፤ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎች

የማእከላዊ መንግሥትና የብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች የጋራ ገቢዎችን የሚወስን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሆነ ኮሚቴ እንደሚቋቋም በአዋጅ ቁጥር 33/85 ተደንግጓል። ይህም ኮሚቴ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባሮች አሉት።

- የማእከላዊ መንግሥትና የብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች የጋራ ገቢዎች በምን ያህል መጠን እንደሚከፋፈሉ መወሰን
- በገቢ ክፍፍል ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚነሱ አከራካሪ ነጥቦችን ለመፍታት የሚያስችሉ የመፍትሄ እርምጃዎችን መጠቆም
- እንደአስፈላጊነቱ የገቢ አመዳደቡ ስለሚሻሻልበት ወይም ስለሚለወጥበት ሁኔታ እያጠና ከዉሣኔ ሃሣብ ጋር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቅረብ ናቸዉ።

## 9.2 የክልሎች ድጎማ

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚገኘዉ የክልል ኘላንና ልማት መምሪያ የክልሎችን ድጎማ ቀመር የሚያዘጋጅ ሲሆን እንዲመረመርና እንዲፀድቅ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ የክልሎች ድጎማ ሁልግዜም የተጎዱ ክልሎችን በሚጠቅም መልኩ የሚዘጋጅ ሲሆን የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ለክልሎች የሚሰጠዉን ድጎማ የሚያዘጋጀዉ ከሁለት ምንጮች ነዉ፡፡ የክልሎች ቀመር የሚገኘዉ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲፀድቅ ሲሆን ጠቅላላ የክልሎች ድጎማ ግምት ከፊሲካል ኘላን የሚገኝ ነዉ፡፡ በማእከላዊ መንግስት ለክልሎች የሚሰጥ ድጉማ የሚከተሉትን መመዘኛዎችና መቶኛ ያካተተ ነዉ፡፡

- የሕዝብ ብዛት /55 በመቶ/
- ድህነት /10 በመቶ/
- የወጪ ፍላጎት / 20 በመቶ/
- ከበጀት አንፃር የግብር አሰባሰብ /15 በመቶ/

ይህም የሀብት እና የኢኮኖሚ ልማት ደረጃን ያጣመረ በመሆኑ ለፊሲካል ፌዴራሊዝም አደረጃጀት ተሞክሮ ጥንካሬ የሚያስገኝ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ሠንጠረዥ 17

በማእከላዊ መንግስት ለክልሎች የተሰጠ ድጎማ

/በሚልዮን ብር/

| ዓ.ም | ትግራይ | አፋር | አማር | ኦሮሚያ | ሶማሊያ | ቤንሻንጉል | ደ.ብ.ብ.ሕ | ጋምቤላ | ሐረር | አ.አ | ድሬዳዋ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | | 12 | 13 | 14 | | |
| 1986 | 187.17 | 93.34 | 384.95 | 585.37 | 59.92 | 70.21 | 336.87 | 53.72 | 8.06 | 111.17 | 1.10 | 1891.88 |
| 1987 | 261.61 | 71.73 | 564.40 | 646.20 | 63.91 | 71.18 | 470.63 | 56.40 | 30.60 | 90.26 | 3.00 | 2329.92 |
| 1988 | 261.60 | 82.69 | 614.52 | 709.68 | 105.14 | 65.14 | 469.81 | 78.64 | 29.40 | 45.63 | 8.70 | 2470.95 |
| 1989 | 278.13 | 136.64 | 706.63 | 880.70 | 124.05 | 107.03 | 516.95 | 88.29 | 38.00 | 1.18 | 14.17 | 2891.77 |
| 1990 | 265.97 | 172.20 | 722.46 | 836.55 | 203.80 | 162.06 | 562.72 | 65.50 | 76.65 | 2.22 | 31.94 | 3102.07 |
| 1991 | 229.43 | 209.74 | 677.52 | 879.18 | 213.10 | 142.99 | 563.63 | 130.62 | 40.98 | 1.02 | 33.19 | 3121.40 |
| 1992 | 188.83 | 170.86 | 532.40 | 613.42 | 218.06 | 111.99 | 430.02 | 97.58 | 58.64 | 0.00 | 16.73 | 2438.53 |
| አማካይ | 238.96 | 133.9 | 600.41 | 735.87 | 141.1 | 104.37 | 478.7 | 81.54 | 40.3 | 35.93 | 15.5 | 2606.65 |

ሠንጠረዥ 18

ድርሻ / በፐርሰንት /

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1993/94 | 9.89 | 4.93 | 20.35 | 30.94 | 3.17 | 3.71 | 17.81 | 2.84 | 0.43 | 5.88 | 0.06 | 100 |
| 1994/95 | 11.23 | 3.08 | 24.22 | 27.73 | 2.74 | 3.06 | 20.20 | 2.42 | 1.31 | 3.87 | 0.13 | 100 |
| 1995/96 | 10.59 | 3.35 | 24.87 | 28.72 | 4.26 | 2.64 | 19.01 | 3.18 | 1.19 | 1.85 | 0.35 | 100 |
| 1996/97 | 9.62 | 4.73 | 24.44 | 30.46 | 4.29 | 3.70 | 17.88 | 3.05 | 1.31 | 0.04 | 0.49 | 100 |
| 1997/98 | 8.57 | 5.55 | 23.29 | 26.97 | 6.57 | 5.22 | 18.14 | 2.11 | 2.47 | 0.07 | 1.03 | 100 |
| 1998/99 | 7.35 | 6.72 | 21.71 | 28.17 | 6.83 | 4.58 | 18.06 | 4.18 | 1.31 | 0.03 | 1.06 | 100 |
| 1999/00 | 7.74 | 7.01 | 21.83 | 25.16 | 8.94 | 4.59 | 17.63 | 4.00 | 2.40 | 0.00 | 0.69 | 100 |
| አማካይ | 9.28 | 5.05 | 22.96 | 28.31 | 5.26 | 3.93 | 18.39 | 3.11 | 1.49 | 1.68 | 0.54 | 100 |

ምንጭ ገንዘብ ሚኒስቴ

## 9.3 በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን የአወባል ወረዳ የበጀት አመዳደብ /በኢትዮጵያ የሚገኘዉ የአለም ባንክ ቢሮ በመጋቢት 1992 ካጠናዉ የተወሰደ/

በአማራ ክልል ሕገ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 2/1995 መሠረት ክልሉ በአራት ደረጃዎች የተከፋፈለ ነዉ:: እነሱም 1ኛ ክልል ምክር ቤት 2ኛ ዞን መስተዳድር 3ኛ ወረዳ ምክር ቤትና 4ኛ ቀበሌ መስተዳድር ናቸዉ::

አወባል ወረዳ በአማራ ክልል በሚገኘዉ ምስራቅ ጎጃም ዞን ዉስጥ ከሚገኙት 14 ወረዳዎች አንዱ ሲሆን ከዞኑ ዋና ከተማ ከደ/ማርቆስ በ40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛ ል:: የሕዝብ ብዛቱም 165312 ሲሆን 81100 ወንዶችና 84412 ሴቶች ይገኙበታል:: ወረዳዉ በ37 የገጠር ቀበሌዎችና በ3 የከተማ ቀበሌዎች የተከፋፈለ ነዉ:: ከጠቅላላዉ ሕዝብ 90% በግብርና የሚተዳደር ሲሆን 10 ፐርሰንት በ3ቱ የከተማ ቀበሌዎች ኗሪ ነዉ::

የአማራ ክልል ሕገ መንግስት በአንቀፁ 79 መሠረት በስሩ ላሉ ወረዳዎች የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ፤ የእርሻ ገቢ ግብርና የንግድ ታክስ እንዲጥሉና እንዲሰበስቡ ስልጣን የሰጠ ሲሆን በተግባር ግን ወረዳ ፤ ዞኑና ክልሉች ጋር በመወያየት የሚፈፀም ነዉ:: የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ከ10 እስከ 20 ብር የሚደርስ ሲሆን የእርሻ ስራ ገቢ ግብርም ከ10 እስከ 25 የኢትዮጵያ ብር ይደርሳል::

ክልሉ ለዞኑ የሚያደርገዉ ድጎማ የፌዴራል መንግስት የሚጠቀምበትን ቀመር መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህም የሕዝብ ብዛት፤ የመሰረተ ልማት ደረጃና የግብር አሰባሰብ አቅምን መሠረት ያደረገ ነዉ:: ምስራቅ ጎጃም ዞን በ1991 ዓ.ም ከአማራ ክልል ካገኘዉ ድጎማ ዉስጥ 32 ፐርሰንት ከመደበኛ 37 ፐርሰንት ከካፒታል በጀት ለዞኑ ያስቀረ ሲሆን ቀሪዉን ለ14ቱ ወረዳዎች አከፋፍሏል:: ለ14ቱ ወረዳዎች እኩል የሆነ ክፍፍል እንደሚያደርግ ቢገለጽም በ1991 ለአወባል ወረዳ የተመደበዉ የወረዳዎች ድርሻ ለ14ቱ ከተከፈለ በኃላ የተገኘዉን 65 ፐርሰንት ብቻ ነዉ:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 2.28 ሚልዮን ብር ከዞኑ መስተዳድር ለወረዳዉ ድጎማ የተሰጠ ሲሆን 32 ፐርሰንት ለልማት ኘሮጀክቶች ሲዉል 68 ፐርሰንት ለደመወዝና ስራ ማስኬጃ ዉሏል:: በአጠቃላይ በ1991 ዓ.ም የወረዳዉ ገቢ ድጎማና የዉስጥ ገቢን ጨምሮ 3.84 ሚሊዮን ብር ሲሆን ከዉስጥ ገቢ የተገኘዉ 41 ፐርሰንት ነዉ / ሠንጠረዥ 17/

ሠንጠረዥ 19


የአወባል ወረዳ የ1991 በጀት ዓመት የበጀት ምደባ

| የዉስጥ ገቢ | ጠቅላላ ወጪ | | | | የዉስጥ ገቢ /ድርሻ %/ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | | ካፒታል | ድምር | |
| | ደመወዝ | ስራ ማስኬጃ | | | |
| 1.56 | 2.47 | 0.63 | 0.74** | 3.84 | 50 |

** ከሕዝብ በአይነትና በጉልበት የተገኘዉን አይጨምርም

የካፒታል ወጪዉ ከጠቅላላ ወጪዉ 19 ፐርሰንት ሲሆን ከዚህም ዉስጥ አብዛኛዉ ገንዘብ ከሲዉዲን አለም አቀፍ የልማት ድርጅት የተገኘ ነዉ። ከወረዳዉ የታክስ ገቢ የተገኘዉ 1.56 ሚሊዮን ብር ሲሆን በአይነትና በጉልበት ከሕዝቡ የተገኘዉም ለልማት ፕሮጀክቶች እንደዋለም ተገምቷል። በ1991 ዓ.ም በአወባል ወረዳ የነበረዉን የበጀት አመዳደብ በሚቀጥለዉ ሥዕል ይመልከቱ

## በ1991 ዓ.ም በአወባል ወረዳ የነበረዉ የበጀት አመዳደብ



## 10. የመንግስት የዕቃና አገልግሎት ግዥ

ገንዘብ ሚኒስቴር የሕዝብ ሀብት በተገቢወ፟ መንገድና ኢኮኖሚያካል በሆነ የወጪ አጠቃቀም እንዲመራ የማድረግ ኃላፊነት አለበት:: በመሆኑም በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚካሄዳ፟ትን የሀገር ዉስጥ ግዥዎች ከ5000ሺ፟ ብር በላይ ስ፟ሆኑና የዉጭ አገር ግዥዎች ደግሞ ከሁለት ሚሊዩን ብር በላይ ሲሆኑ በገንዘብ ሚኒስቴር በሚገኘዉ የመንግስት ዕቃ ግዥ መምሪያ ይጠናል:: መንግስት በየዓመቱ ከሚያመድበዉ በጀት ዉስጥ ከፍተኛዉን ድርሻ የሚይዘዉ ወጪ የመንግስት ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲሆን ከመንግስት ዓመታዊ በጀት ዉስጥ ለግዥ የሚዉለዉ ወጪ ከ40 እስከ 50 ፐርሰንት ይደርሳል:: የመንግስት ግዥ ከቢሮ ወ፟ስጥ አላቂ ዕቃዎች እስከ ግዙፍ ቋሚ ዕቃዎችና እንዳ፟ሁም የኮንስትራክሽን ግንባታና የአገልግሎት ግዥዎች ያለዉን ያጠቃልላል::

- የአገልግሎት ግዥ ማለት በሰዉ ወይም በመሳሪያ አማካኝነት የሚገኝ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል::
- የምክር አገልግሎት /Consultancy service/
- የጥገና አገልግሎት /Maintenance service/
- የማስታወቂያ ሥራ አገልግሎት/Advertising service/
- የኪራይ አገልግሎት/Renting service/
- የግዥ አገልግሎት /Procurement service/
- የትራንስፖርት አገልግሎት /Transport service/

በመሆኑም መንግስት አነስተኛ ወጪ ወፈፀሙን ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለዉ ዕቃና አገልግሎት ማግኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል:: ይህም ሲሆን የሚችለዉ ብቃትና ተአማኒነት ያላቸዉ አቅራቢዎች ሲኖሩ ብቻ ነዉ:: የገንዘብ ሚኒስትሩ በኢፌ.ዴ.መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 69 እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት አስፈሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 19 በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የግዥ መመሪያ አዉጥቷል::

1. በመንግሥት ግዥ ዉስጥ ለመሳተፊ የሚፈልግ ማናቸዉም አቅራቢ እንደአግባብነቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ከሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል። የዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝ በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 16/1989 አንቀጽ 67 የሚከተለዉን ደንግጓል።
2. የገንዘብ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸዉ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የአገር ዉስጥ ግዥዎችን በሚመለከት የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣
3. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የኮ ስትራክሽን ሥራ ዉሎችን በተመለከተ የአቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጃል ፣ይይዛል፣
4. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች ግዥን በተመለከተ የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል።

## 10.1 የግዥ ዓላማዎች

- የሀገር ሀብትን ዉጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የመንግስት ግዥ በሚከተሉት መሠረታዊ የግዥ ዓላማዎችና ፖሊሲዎች ላይ ተመስርቶ መካሄድ ይኖርበታል። /መልዕክተ ንጥይ ቅጽ 1 ቁጥር 3/
- ቁጠባ
- ቅልጥፍና እና ብቃት
- ከአድልዎ ነፃ መሆን
- ግልጽነት

ለሕዝብ ተጠሪነት ወይም ተጠያቂነት

### 10.1.1 ቁጠባ /Economy/

- ግዥን በግልጽ ጨረታ መፈፀም ቁጠባ ከሚያስገኙ መንገዶች አንዱ እንደሆነ የማያነገር ስፔሆን ይህም የሚሆነዉ
- የጨረታ ማስታወቂያን በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ግልጽ በሆነ መንገድ በማወጥጣት፣
- ለጨረታ ዝግጅት በቂና ተመጣጣኝ ጊዜ በመስጠት፣

- ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንገድ ስፔስፊኬሽን በማዘጋጀት፤ እና

በግልጽና በማያሻማ መንገድ ተጫራቾችን አወዳድሮ አሸናፊዉን ለመምረጥ የሚያስችል የማወዳደሪያ መስፈርቶችን መምረጥንና ይህንንም የጨረታ ሰነድ ወፒስጥ በማካተት ተጫራቾች በቅድሚያ እንዲያወፒቁት ማድረግ ነዉ፡፡

ተጫራቾች በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ላይ ሙሉ እምነት እንዲያሳድሩ በማድረግ የጨረታ ተሳታፊዎችን ቁጥር መጨመር እና ከብዙ ተሳትፎና ዉድድር የተሻለ ጥራት እና የዋጋ ቅናሽ ማግኘት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዋና መስሪያ ቤቶች በሥራቸዉ ከሚገኙ ቅርንጫፎቻቸዉ ጋር በጋራ የማፓፈልጓቸወፒን ዕቃዎች አጠቃሉ መግዛት ቁጠባን ከሚያስገኙ መንገዶች ሌላዉ ይሆናል፡፡

### 10.1.2. ቅልጥፍናና ብቃት /Efficiency /

በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ያልተማከለ አሠራርን /Decentralization/ መፍጠር የግዥ ተግባርን ቀልጣፋ ለማድረግ የሚረዳ ሲሆን አሳስፈላጊ የሆኑና የተንዛዙ የቁጥጥር ሥርዓቶችንና ሪፖርት የሚደረግላቸዉን አካላት መቀነስ ማለት ነዉ፡፡

### 10.1.3. ከአድል ነፃ የሆነ አሠራር መፍጠር /Non-discrimination/

ግልጽ ጨረታ ከአድልዎ ነፃ ለሆነ አሠራር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለዉ ሲሆን ከአድል ነፃ የሆነ አሠራር ማለት በአጭሩ ተጫራቾችን በሙሉ በእ ፒል ዓይን ማየት ማለት ነዉ፡፡

### 10.1.4. ግልጽነት /Transparency/

- በግዥ ሂፓደት ዉስጥ ግልጽነት /Transparency/ እንዲኖር ማድረግ ማለት የግዥ አሠራርን ለሕዝብ ግልጽ ማድረግና ለቁጥጥር አመቺ የሆነፒ ሥርዓቶችን መዘርጋት ማለት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ግልጽነት ማለት
- የግዥ ደንብና መመሪያ መኖር!
- የተሞላ የጨረታ ሠነድ ማዘጋጀትን፤ እና

ከጨረታ አከፋፈት ጀምሮ በየደረጃዉ ያሉ የጨረታ ግምገማና ዉድድሮችን ለሕዝብ እይታ ግልጽ የማድረግ ሁነፓታን የማፓጠይቅ ሲሆን

በተጨማሪም ዕቃ አቅራቢዎቹ በጨረታዉ የተሸነፋበትን ምክንያት እንዲያዉቁና በጨረታ ዉሳኔዉ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ አበፖቱታ የማቅረብ መብታቸዉ እንዲረጋገጥ ማድረጉ ለአሰራር ግልጽነት መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

### 10.1.5. ለህዝብ ተጠያቂነት ወይም ተጠሪነት /Accountability/

ለሕዝብ ተጠሪነትን ለመግለጽ ተገቢ ባልሆነና መንግስትን ለኪሳራ በሚዳርግ እንዲሁም የመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ በሚፃረር መልክ ግዥ ሠራተኞች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መወሰድ ያስፈልጋል፡፡

## ማጠቃለያ

የመንግስት ፋይናንስ /Public finance/ የመንግሥት ገቢና ወጪን የሚመለከት ሲሆን እነዚህን ዘርፎች በፖሊሲ፣ በአፈፃፀም እና አፈፃፀሙን የሚመሩ የሕግ ማዕቀፎች በማቋቋም በተገቢዉ መንገድ ለመምራት እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነዉ። በተለይም የመንግስትን ገቢ ለማጠናከር የተለያዩ የአፈፃፀም ዘዴዎችን መዘርጋትና ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶችን ብቃታና ዉጤታማነትን በሚያረጋግጥ አኳኃን ማደራጀት አስፈላጊ ነዉ። የገቢ መስሪያ ቤቶችን በማደራጀት ረገድ በሰዉ ኃይል፣ በዘመናዊ የመረጃ ፍሰት ሥርዓትና አስፈፃሚ በሆኑ መዋቅሮች እንዲጠናከሩ እየተደረገ ነዉ።

እንደ ኢትዮጵያ ላለ ታዳጊ አገር መንግሥት ለኢኮኖሚ ልማት፣ ለማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋት፣ ለባሕል ዕድገት፣ ለመከላከያና ደህንነት፣ ለፍትህ መስፈን፣ ለአካባቢ ጥበቃ በአጠቃላይ ለሕዝብ የኑሮ መሻሻል እና ለአገር ብልፅግና መሣካት የሚያወጣዉን ፖሊሲ እንዲሁም የማንቀሳቀሰዉን ዕቅድ ዕዉን ለማድረግ ግብር ከፍተኛ ድርሻ አለዉ። በመሆኑም ኢኮኖሚዉ ሊያመነጭ የሚችለውን የግብር መጠን ለመሰብሰብና ለማሣደግ ዉጤታማ የሆነ የታክስ አስተዳደር አስፈላጊ ነዉ።

የታክስ አስተዳደሩን ለማጠናከር የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥ፣ የቁርጥ ግብር፣ የግብር ሂሣብ መርመራና አወሳሰን፣ የግብር ሂሣብ ምርመራና አወሳሰን፣ የግብር ሂሣብ አያያዝና የወጪዝፍ ግብር አስተዳደር፣ እና የተጨማሪ እሴት /Value Added Tax/ ጥናት ላይ ትኩረት እየተሰጠበት ያለ ነዉ።

በዚህ የበጀት ማኑዋል አሁን እየተሠራበት ያለዉን የበጀት ሂደትና በበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂዉ መሠረት የተዘጋጀዉን የበጀት ሂደት ለማሳየት ተሞክሯል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አካል የሆነዉ የበጀት ማሻሻያ ስትራቴጂ በአሁኑ ወቅት የሚሠራበትን የበጀት አስተዳደር የሚያሻሽል ሲሆን እስከአሁን የሚሠራበትን ግን ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር አይደለም። አሁን እየተሠራበት ያለዉ የበጀት አሠራር ድክመት ቢኖርበትም ብዙ ጠንካራ ጎኖች አሉት እነሱም የበጀት አዋጅ ሳይወጣ ዉጪ ብደርን የማያዉቅ ሲሆን ሀብትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት /line item budgeting system/ ያለዉ ነዉ። የተፈቀደ በጀቶር ሳዳያወጣ መክፈል መቻሉ ከጠንካራ ጎኑ አንዱ

ነዉ:: ሌላዉ ጠንካራ ጎነር በጀት በተደጋጋሚ /supplement budget/ አለመታወጁ ነው::

1. የበጀት ማሻሻያ ስትራቴጃፔ አራት ዓላማዎች ያሉት ሲሆን እነሱም
2. በወጪ ማዕከል ላይ የተመሠረተ በጀትን ሥራ ላይ የሚያወፔል ወጥ የሆነ የበጀት አመዳደብ ሥርዕት መዘርጋት
3. ለወጪና ለገቢ አዳፔስ የሂፓሳብ አወቃቀር ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲወፔል ማድረግ
4. የፋይናንስ ዕቅድን ከበጀት አፈቃቀድ ጋር የሚያገናኝ አዲስ የፋይናንስ ዕቅድ የጊዜ ሠሌዳ እንዲኖር ማድረግና በጀቱን ከዝግጅት እስከ መፍቀድ እና የአፈፃፀም መርሃ ግብር እስከ ማዘጋጀት ድረስ የሚያልፍበትን የተለያዩ ደረጃዎች እና የሚጠናቀቁበትን የጊዘፖ ሠሌደ መወሰን ሲሆን

አዳዳፔስ የበጀት አደረጃጀት ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅፃችን ሥራ ላይ እንዲዉል የሚያደርግ ነዉ::